# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 108 ታኅሣሥ 18 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# በውጭ ሀገር ለሚኖሩ 2ኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን
## የቀረበው ጥሪ መነሻ ሀገራቸውን እንዲያውቁ እድል ይሰጣል



ፎቶ፡ በሔኖክ አብርሃ

አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በውጭ ሀገር ለሚኖሩ የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ያቀረቡት ጥሪ ዳያስፖራዎች መነሻ ሀገራቸውን እንዲያውቁ እድል የሚሰጥ ነው ሲሉ የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ ገለጹ፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በሦስት ዙሮች ወደ ሀገር ቤት እንዲገቡ ጥሪ ማቅረባቸውን ተከትሎ የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ በሰጡት መግለጫ እንዳመለከቱት፤ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥሪ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያዊያን መነሻ ሀገራቸውን እንዲያውቁና በማንነታቸው እንዲኮሩ የሚያስችል ነው፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተደረገው ጥሪ የትውልዱን ቅብብሎሽ የሚያስቀጥል ነው ያሉት አምባሳደር ናሲሴ፤ ዳያስፖራዎች ከወላጆቻቸው ጋር ሀገር እንዲተዋወቁና እንዲተሳሰሩ የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

ቀደም ሲል ከኢትዮጵያ የሄዱ የሁለተኛ ትውልድ ወላጆች ወደ ሀገር ቤት እንዲመጡና ግንኙነት እንዲፈጥሩ ሲሠራ መቆየቱን አስታውሰው፤ የትውልዱን ቅብብሎሽ ለማስቀጠል ለሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያዊያን መጥራት ማስፈለጉን ገልጸዋል፡፡

ለሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ከወላጆቻቸው ሀገር ጋር ቁርኝት እንዲፈጥሩ፣ መነሻ ሀገራቸውን በአግባቡ እንዲረዱና በማንነታቸው እንዲኮሩ የሚያስችል መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሯ፤

በውጭ ሀገር ለሚኖሩ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል






## በየሩብ ዓመቱ
### በሕገወጥ ንግድ ከ106 ሺህ በላይ የቁም እንስሳት ከሀገር ይወጣሉ

ገጽ 6

# የዓድዋው አሻራ

**ማርቆስ በላይ**

ፒያሳ የአዲስ አበባ እምብርት ናት። በአዲስ አበባ የምስረታ ታሪክ ቀደምት ነዋሪዎች በብዛት የከተሙባት መንደር። የከተማዋ ከንቲባዎች፣ የካቢኔና የምክር ቤት አባላት ስለከተማዋ የሚወያዩበት እና ውሳኔዎችን የሚያሳልፉበት ስፍራም ናት። ይህ ብቻ አይደለም፤ በየትኛውም አቅጣጫ የሚገኙ የሀገራችን አካባቢዎችን ርቀት ለመለካት መነሻ ቦታም ናት።

እነሆ በአሁኑ ወቅት ታዲያ በዚህ ታሪካዊ ስፍራ አንድ ትልቅ የታሪክ አሻራ እየተቀመጠ ነው- የዓድዋ ዜሮ ኪሎ ሜትር ፕሮጀክት።

የፕሮጀክቱ አስተባባሪዎች እንደሚገልጹት፤ ስያሜው "ዓድዋ ዜሮ ኪሎ ሜትር ፕሮጀክት" ሲሆን ይህም የሆነው ሁሉንም የሀገሪቱ አካባቢዎች ርቀት ለመለካት መነሻው ከዚህ በመሆኑ ነው።

የዓድዋ ፕሮጀክት ከዛሬ 128 ዓመታት በፊት ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ቅኝ ገዢዎችን የመከቱበትና የጥቁር ሕዝቦችን አንገት ቀና ያደረገውን የዓድዋ ድል የሚያስታውስ ትልቅ ፕሮጀክት የተገነባበት ነው።

የመላው ኢትዮጵያውያን ድል የሆነው ዓድዋ በተለይም ለአፍሪካውያን በግልጽ የታየ የነጻነት ነጸብራቅ ነው። የዓድዋ ድል ጥቁር የሰው ዘር ከሁሉም የሰው ዘር ጋር ዕኩል መሆኑን፤ በደምና በአጥንት የተጻፈበት የመላው የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ አንጸባራቂ የጋራ ድል ነው።

የዓድዋው... ወደ ገጽ 6 ዞሯል





## "በቀጣዮቹ ሦስት ወራት ለስድስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ተረጂዎች ድጋፍ ይደረጋል"

- ኮሚሽነር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር

**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣዮቹ ሦስት ወራት ለስድስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ተረጂዎች ድጋፍ ይደረጋል ሲሉ የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) አስታወቁ። በድርቅና በጎርፍ ለተጎዱ ወገኖች ከሐምሌ 2015 ጀምሮ እስከ

"በቀጣዮቹ ሦስት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል









አቶ ሀብታሙ ኃይለሚካኤል

## ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች በሦስት ወራት ከዘጠኝ ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት በሶስት ወራት ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ከዘጠኝ ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ መገኘቱን የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እና ይዞታ አስተዳደር ገለጸ።

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እና ይዞታ አስተዳደር የ2016 ዓ.ም የሩብ ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት ለሕዝብ ተወካዮች ባቀረበበት ወቅት፤ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ኃይለሚካኤል እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ከዘጠኝ ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል።

በሪፖርቱ ላይ እንደተገለጸው፤ በሩብ ዓመቱ ለማግኘት የታቀደው 11 ነጥብ 86 ቢሊዮን ብር ሲሆን፤ ሊገኝ የቻለው ዘጠኝ ቢሊዬን ብር ነው።

ይህም ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር አራት በመቶ ብልጫ እደንዳለው ተገልጿል።

አቶ ሀብታሙ እንደገለጹት፤ የዘጠኙም የልማት ድርጅቶች ገቢ እያደገ መጥቷል። በዚህም በ2013 ዓ.ም አጠቃላይ ገቢያቸው 10 ቢሊዮን፣ በ2014 35 ቢሊዮን፣ 2015 45 ቢሊዮን ብር መሆን ችሏል። በተያዘው ዓመት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ደርሷል።

ከትርፍ አንጻርም 2014 በጀት ዓመት የዘጠኙ የልማት ድርጅቶች ትርፍ 4 ነጥብ 3 ቢሊዬን ብር ሲሆን በ2015 ወደ ስምንት ቢሊዮን መድረስ ችሏል። በዘንድሮው ዓመት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 807 ሚሊዮን እንደሆነ ተናግረዋል።

በተጨማሪም ለአምስት ዓመት የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት አስተዳደሩ መሰረታዊ አቅጣጫዎችን አስቀምጦ እየሰራ ይገኛል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በዚህም የልማት ድርጅቶቹ የአስተዳደር ስርዓታቸው እና ገንዘብ የማንቀሳቀስ ተግባራቸውን የማዘመን ስራ ተሰርቷል ብለዋል።

በየትኞቹ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ትኩረት ተደርጎ መሰራት አለበት የሚለውን በመለየትም፤ ድርጅቶቹ ገቢ እንዲያስገኙ ለማድርግ ተሰርቷል ሲሉ አስረድተዋል።

በዚህም ትልቅ ችግር ያለባቸውን የልማት ድርጅቶች ችግራቸውን የማቃለል፤ ከፍተኛ እዳ ያለባቸውን የመደገፍ ስራ የተሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በአጠቃላይ የህዝብ ከሚለው እሳቤ በመውጣት ሀብት በማፍራት ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራቱን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት በአፍሪካ አንደኛ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ አራተኛ መሆን መቻሉን ለማሳያነት አንስተዋል።

ልማት ባንክም በኪሳራ ከመዘጋት ተርፎ ሰፊ የብድር አቅርቦት እያደረገ የሚገኝ መሆኑን አንስተው፤ ኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ከሀብት አባካኝነት በመውጣት ሀብት እያስገባ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

# ቋሚ ኮሚቴው ሚኒስቴሩ የፋይናንስ ጉድለቶቹን እንዲያስተካክል አሳሰበ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስአበባ፡-የቱሪዝም ሚኒስቴር በኦዲት የተገኘበት የፋይናንስ ጉድለቶች አስተካክሎ እንዲያሳውቅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ።

የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የቱሪዝም ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ትናንት ገምግሟል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ወይዘሮ አራሬ ሞሲሳ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተለያዩ የኦዲት ግኝት ጉድለቶች ተገኝተውበታል።

ከፋይናንስ አሠራር ውጪ ለቤት እድሳት የዋለ ገንዘብ፣ ያለአግባብ የተከፈሉ ክፍያዎች፣ የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ባላገናዘበ መልኩ የወጡ የተጋነኑ ወጪዎች እንዲሁም የመሥሪያ ቤቱን ንብረት ይዘው ሥራ የለቀቁ ሰዎች ላይ ሚኒስቴሩ ርምጃ ወስዶ ሪፖርት እንዲያቀርብ አሳስበዋል።

በ2014 በጀት ዓመት ከተመደበው በጀት ውስጥ 19 ሚሊዮን 361 ሺህ ብር በላይ ገንዘብ ሥራ ላይ አለመዋሉን አስታውቀው፤ በኦዲት ሪፖርቱ የተገኘው ገንዘብ ምክንያቱ እንዲብራራ ጠይቀዋል።

በተለይ ለሦስት ሾፌሮች የፕሮቶኮል ወጪ 322 ሺህ 200 ብር የተጋነነ ግዥ መፈጸሙን የጠቆሙት ወይዘሮ አራሬ፤ ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የተሰጠ የኃላፊ ቤት ዕድሳት 431 ሺህ 250 ብር መውጣቱ አግባብ እንዳልሆነ ገልጸዋል።

ቋሚ ኮሚቴው ባቀረበው የጽሁፍ ጥያቄ የዕቃው አይነት ያልተገለጸ የፈርኒቸር ግዥ 30 ሚሊዮን ብር ወጪ መደረጉን በመጥቀስ ሚኒስቴሩ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ተጠይቋል።

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያሉ ክፍተቶችን በመገምገም እንዲያስተካክል የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የቤት ሥራ ወስዶ መስራት እንዳለበት



ወይዘሮ አራሬ ሞሲሳ



አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ

ወይዘሮ አራሬ አመላክተው፤ ያለአግባብ የወጡ የነዳጅ ወጪ ተስተካክሎ ሪፖርት መቅረብ እንዳለበትም ገልጸዋል።

ሚኒስቴሩ የተገኙበትን የሂሳብ ኦዲት በፋይናንሱ ላይ ያለው ክፍተት አስተዳደራዊ ርምጃ ወስዶ ግኝቶች እስከ መጋቢት ወር 2016 ዓ.ም ድረስ ለቋሚ ኮሚቴው ሪፖርት እንዲቀርብ አሳስበዋል።

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ዋና ኦዲተር ወይዘሮ መሰረት ዳምጤ በበኩላቸው፤ በሚኒስቴሩ በኩል ለተለያዩ ሥራዎች ክፍያዎች በወቅቱ ባለመከፈላቸው ተጨማሪ ወጪዎች ከመንግሥት ካዝና ያለአግባብ ወጪ ሆኗል ብለዋል።

በርካታ የሚኒስቴሩ ወጪዎች ከፋይናንስ አሠራር ውጪ የተከናወኑ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ቱሪዝም ሚኒስቴር ያለምንም መሐንዲስ ማረጋገጫ ለግንባታዎች በቀጥታ ክፍያ ሲፈጽም እንደነበር አስረድተዋል።

የተለያዩ ግዢዎች ያለ ውድድር መፈጸማቸውን አስታውቀው፤ ይህም መንግሥት ከጨረታ የሚያገኘውን ገንዘብ ከማሳጣት በተጨማሪ ለብልሹ አሠራሮች መንገድ የሚከፍት መሆኑን ጠቁመዋል።

የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ በበኩላቸው በሰጡት ምላሽ እንደተናገሩት፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የፋይናንስ ሥርዓት ክፍተትና የባለሙያዎች ውስንነት እንደነበረበት ገልጸዋል።

እንደሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የባለሙያዎች የአቅም ውስንነት በተለያዩ ስልጠናዎች ለማብቃት ተሰርቷል ያሉት ሚኒስትሯ፤ እስካሁን የተሰሩ ማስተካከያዎች በቀጣዩ የኦዲት ግኝት ሪፖርት ላይ በጎ ውጤት እንደሚያመጣ አስረድተዋል።

በሥራ ላይ ያልዋሉ በጀቶች በባለሙያ ክፍተትና በቢሮ እጥረት ምክንያት የተፈጠረ መሆኑን ጠቁመው፤ ለሾፌሮች የፕሮቶኮል የወጣው ወጪ ወጥ አሠራር ባለመኖሩ የተፈጠረ መሆኑን ተናግረዋል።

የፈርኒቸር ግዥውን በተመለከተ አስፈላጊው የተገዙ ዕቃዎች ሰነድ በሚኒስቴር በመኖሩ በማንኛውም ጊዜ ሊጣራ እንደሚችል አመላክተዋል።

# በማዕከላዊ ኢትዮጵያ 17 ሚሊዮን ኩንታል የመኸር ምርት ተሰበሰበ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በ2015/16 የመኸር እርሻ 17 ሚሊዮን ኩንታል የሰብል ምርት መሰብሰቡን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል አሳወቀ። በክልሉ ከመኸር ምርት ስብሰባው ጎን ለጎን የበጋ መስኖ ልማትን በሚመለከትም 141 ሺህ ሄክታር ለማልማት ታቅዶ ከ70 በመቶ በላዩ በሰብል ዘር ተሸፍኗልም ተብሏል።

በክልሉ በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ልማት ክላስተር አስተባባሪና የክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡስማን ሱሩር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በ2015/16 የመኸር እርሻ 17 ሚሊዮን ኩንታል የሰብል ምርት መሰብሰብ ተችሏል።

እንደ አቶ ኡስማን ንግግር፤ 445 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ካሉ ከቋሚና ከዓመታዊ ሰብሎች በመሰብሰብ 42 ሚሊዮን ኩንታል ለመሰብሰብ ታቅዶ ነበር። በተሰራው ሥራ እስካሁን ድረስ ከ360 ሺህ ሄክታር ላይ 17 ሚሊዮን ኩንታል የሰብል ምርት መሰብሰብ ተችሏል።

ይህም የእቅዱ 49 በመቶ ያህል ስለመሆኑ አቶ ኡስማን የተናገሩ ሲሆን፤ የፍራፍሬና ሌሎችም ሰብሎች ስብሰባ በቀጣይ የሚሠራ ስለመሆኑ ጠቅሰዋል።

በተቀናጀ መልኩ የተሠሩ የምርት ንቅናቄዎችን በምርት አሰባሰብ እንድገማቸው በሚል የተሠራ ሥራ ስለመኖሩ የጠቀሱት አቶ ኡስማን፤ ከብክነት የፀዳ የጥራት ጉድለት የሌለበት የመኸር ምርት አሰባሰብን ለመከወን ስለመሰራቱና ይህም በከፊል ውጤታማ ስለመሆኑ አመላክተዋል።

በክልሉ የመኸር ሰብል አሰባሰብ በሦስት ዘርፍ ሊታይ እንደሚችል ያመላከቱት አቶ ኡስማን፤ የመጀመሪያው በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ያሉ ዞኖችና ወረዳ ተሰብስቦ ማለቁን ተናግረዋል።

ከስምጥ ሸለቆ ትንሽ ራቅ ያሉ አካባቢዎች ወደ መጠናቀቁ ላይ እንዳሉ ጠቅሰው፤ በደጋማ አካባቢዎች ላይ ገና በጅምር ላይ መሆኑን አብራርተዋል።

ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተከስቶ የምርት አሰባሰብ ሂደቱን ችግር ደቅኖበት እንደነበር ያወሱት አቶ ኡስማን፤ ምርት እንዳይባክን ተማሪዎችን፣ የመንግሥት ሠራተኞችንና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችን በማስተባበር የደረሱ ሰብሎችን የመሰብሰብ ሥራ ተሠርቷል ብለዋል።

ከመኸር ምርት አሰባሰብ ጎን ለጎን የበጋ መስኖ ልማትን በሚመለከትም ስለመሰራታቸው ያመላከቱት አቶ ኡስማን፤ 141 ሺህ ሄክታር ለማልማት ታቅዶ ከ70 በመቶ በላይ በሰብል ዘር ተሸፍኗል ሲሉ ተናግረዋል።

የበጋ መስኖ ልማቱ አትክልት ስራስር ሽንኩርትና የበጋ መስኖ ስንዴን የሚያጠቃልል ስለመሆኑ አቶ ኡስማን ተናግረዋል።



ፎቶ ሐዱሽ አብርሃ

አቶ ኡስማን ሱሩር

ዜና



አቶ ሀብታሙ ታዬ

# ባለፉት አምስት ወራት 139 ሺህ 560 ዩኒት ደም ተሰብስቧል

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት አምስት ወራት 139 ሺህ 560 ዩኒት ደም መሰብሰቡን የኢትዮጵያ ደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት አምስት ወራት በመላ ሀገሪቱ 168 ሺህ 700 ዩኒት ደም ለመሰብሰብ ታቅዶ፤ በአምስት ወራት 139 ሺህ 560 ዩኒት ደም ተሰብስቧል።

አቶ ሀብታሙ እንዳሉት፤ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች በነበረው የጸጥታ መደፍረስ ደም ባንኮች በሚፈለገው ደረጃ ደም ማሰባሰብ ባለመቻላቸው የተያዘውን እቅድ ማሳካት አልተቻለም ብለዋል።

በአምስት ወሩ የተመዘገበው አፈጻጸም ከባለፈው ዓመት የተሻለ ቢሆንም አቅርቦትንና ፍላጎትን ከማመጣጠን አንጻር ጉድለት አለበት ብለዋል።

በክልል ደረጃ ያለው የደም ልገሳ አፈጻጸም በተመለከተ የተወሰኑ ክልሎች ላይ በጸጥታ ምክንያት ደካማ እንቅስቃሴ መኖሩን የተናገሩት አቶ ሀብታሙ፤ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በኦሮሚያና ሶማሌ ክልሎች የተሻለ አፈጻጸም እንዳለ ተናግረዋል።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ሲዳማ እንዲሁም ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የደም ልገሳ አፈጻጸሙ መካከለኛ ሲሆን፤ በአንጻሩ ከዚህ በፊት በርካታ ደም ሲሰበስብ የነበረው አማራ ክልል ደም ባንኮች ባጋጠማቸው የጸጥታ መደፍረስ ዝቅተኛ አፈጻጸም አስመዝግበዋል ብለዋል።

የደም ልገሳው በተጠናከረ ሁኔታ እንዲቀጥል ማዕከል ላይ እየተሠራ ያለው ሥራ አበረታች ቢሆንም፣ በሀገሪቱ ወጥ የሆነ አሰራር እንዲኖር እና ሁሉም ማህበረሰብ የደም ልገሳ ሥራውን ባህል አድርጎ መቀጠል እንዲችል በትኩረት ሊሰራ ይገባል ብለዋል።

ፍላጎትንና አቅርቦትን ለማመጣጠን ሰዎች በበጎ ፈቃድ ደም እንዲለግሱ ግንዛቤያቸውን የማሰደግ እና ከተጠቃሚዎች ፍላጎት ጋር አብሮ የሚያድግ የደም ልገሳ ባህል እንዲኖር እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

የደም ልገሳ ባህሉን ለማዳበር በትምህርት ቤቶች፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ በደም ልገሳ ክበቦች እና ማህበራት ጋር የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት የግንዛቤ ማስጨበጫና የንቅናቄ ሥራዎች መሠራታቸውን ገልጸዋል።

ትምህርት ቤቶች ሲዘጉ፣ በፆሞች እና በበዓላት ወቅት የደም እጥረት እንደሚያጋጥም ያለፉት ተሞክሮዎች ያሳያሉ ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ በቀጣይ ወር ትምህርት ቤቶች ለእረፍት ሲዘጉና በበዓላት መደራረብ ምክንያት የደም እጥረት እንዳያጋጥም ማኅበረሰቡ በበጎ ፈቃድ እንዲለግሱ ይሠራል ብለዋል።

በቀጣይም የደም ልገሳን ባህል የሚያደርግ ማኅበረሰብን መፍጠር እስከሚቻል ድረስ የግንዛቤ ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል።

የደም ማሰባሰብ ሥራ ላይ በርካታ ችግሮች ያጋጥማሉ ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ ሰዎች መስፈርቱን በደንብ ካለማወቃቸው የተነሳ ደም ለመለገስ መፍራታቸው ተጠቃሽ ነው። ይህም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መሥራት እንደሚገባ የሚያመላክት መሆኑን አብራርተዋል።

የሚተካውን ደም በመስጠት የማይተካውን የሰው ልጅ ህይወት ለመለገስ ማኅበረሰቡ በበጎ ፈቃድ ደም እንዲለግሱ ጥሪ አቅርበዋል።

# ኮርፖሬሽኑ ካሉት 177 የኢንዱስትሪ ፓርክ ሼዶች ውስጥ 157ቱ በኢንቨስተሮች ተይዘዋል

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ካሉት 177 ሼዶች መካከል 157ቱ በኢንቨስተሮች መያዛቸውን አስታወቀ። አምስቱ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ሙሉ በሙሉ በአልሚዎች መያዛቸው ተገልጿል።

የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ፤ ከዚህ ቀደም በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ አብዛኛዎቹ ሼዶች ክፍት እንደነበሩ አስታውሰው፤ አሁን ላይ ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ካስገነባቸው 177 ሼዶች ውስጥ 157ቱ በኢንቨስተሮች የተያዙና የተቀሩ 20 ሼዶችም በአዲስ ኢንቨስትመንት እንዲሞሉ በከፍተኛ ጥረት እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

እንደ አቶ አክሊሉ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ከአጎዋ ከቀረጥ ነጻ ዕድል መውጣቷን ተከትሎ ካለፈው አንድ ዓመት በፊት በርካታ ኩባንያዎች የኢንዱስትሪ ፓሪኮችን ለቀው ቢወጡም፤ በኮርፖሬሽኑ በተሠራው የገበያ ማስተዋወቅ በሀገሪቱ ከሚገኙ 12 የፌዴራል የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ አምስቱ ሙሉ በሙሉ በኢንቨስተሮች መሞላታቸውን ጠቁመዋል።

የአዳማ፣ የቦሌ ለሚ፣ የአዲስ፣ የሰመራና የድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ የማኑፋክቸሪንግ ሼዶች ሙሉ በሙሉ በአልሚዎች መያዛቸውን አስታውቀው፤ የአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ የገባ ሲሆን፤ በሰመራና በሌሎች ፓርኮች ላይ የተቀናጀ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አስረድተዋል።

ቀሪዎቹ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ ክፍት የሆኑ 20 ሼዶች በኢንቨስተሮች የሚያዙባቸው መንገዶች ላይ ስምምነት ለመፈጸም በየቀኑ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።



አቶ አክሊሉ ታደሰ

እንደሀገር በሪፎርሙ የተሰሩ ሥራዎች፣ የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት፣ በማክሮ ኢኮኖሚው ዘርፍ የተደረጉ መሻሻሎችና ሌሎችም የተፈጠሩ ምቹ አጋጣሚዎች ተደምረው በኢንቨስትመንቱ ላይ ከፍተኛ መነቃቃት መፈጠሩን አቶ አክሊሉ ተናግረዋል።

ኮርፖሬሽኑ በአውሮፓ፣ በእሲያና በሌሎች አህጉራት የሚገኙ ገበያዎችን የሚከታተል ቡድን አዋቅሮ ኢንቨስተሮችን ካሉበት ጠይቆ የማምጣት ሥራ እያከናወነ መሆኑን አስታውቀዋል።

እንደ አቶ አክሊሉ ገለጻ፤ ችግር በተፈጠረ ቁጥር ጓዙን ጠቅልሎ የሚሄድ የውጭ ኢንቨስተር ላይ ጥገኛ ሆኖ መቆየት አስፈላጊ ባለመሆኑ፤ የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ ያለበትን የፋይናንስና የክህሎት ጉድለት ለመሙላት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በጋራ እየሠራ ይገኛል።

ካለፈው ዓመትና በ2016 በጀት ዓመት እስካሁን ወደ ሥራ ከገቡ ኢንቨስተሮች ከ50 በመቶ በላዩ የሀገር ውስጥ አምራቾች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የግብርና ምርቶች ማቀነባበር መጀመሩ ካምፓኒዎቹ ከአርሶ አደሮች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ተደርጓል ያሉት አቶ አክሊሉ፤ በዚህም ከ70 ሺህ በላይ የባሌና አርሲ አርሶ አደሮች በቦሌ የኢንዱስትሪ ፓርክ ከሚገኘው የቢራ ገብስ አምራች ድርጅት ጋር ትስስር መፍጠራቸውን አመላክተዋል።

በደብረብርሃን ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገኘው ብቅል አምራች ኩባንያ ከ50 ሺህ በላይ አርሶ አደሮች ጋር አብሮ እየሠራ ሲሆን፤ በጅማ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገኘው የዘይት አምራች ኩባንያ ደግሞ በሺዎች የሚቆጠሩ የአካባቢው አርሶ አደሮች የአቮካዶ ምርት እየተረከበ መሆኑን አስረድተዋል።

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ከ80 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን ያነሱት ሥራ አስፈጻሚው፤ ለአምራቾች አዳዲስ ገበያ የማፈላለግና የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

# ‘ሁሉም ለስብሰባ አዳማ ናቸው’ የሚባልበት ተቋም

ጌትነት ተስፋማርያም




ቢሮው ጠዋት ከሦስት እስከ አምስት ሰዓት ድረስ ብቻ አዳዲስ እንግዶቹን ያስተናግዳል፤ ድንገት ሳት ብሎት አምስት ሰዓት ከአምስት ደቂቃ የመጣ ሰው “ነገ ና” ነው የሚባለው። እሱም ቅዳሜና እሁድ ካልሆነ ነው። በየቀኑ በርካቶች የጠፋባቸውን አሊያም በተለያዩ መንገድ የተበላሸባቸውን የትምህርት ማስረጃ ለማውጣት የተቋሙ በር ላይ ሰልፍ ይይዛሉ።

የቢሮው ሠራተኞች ታሽተው ተጎሽተው ሦስት ሰዓት ላይ ሥራ ሲጀምሩ ግን ሁሉም ተገልጋይ ወደአንድ ጠባብ አዳራሽ እንዲገባ ይደረግና የሚሞላ ፎርም ይሰጠዋል። ፎርሙ በኦንላይን አማራጭም ሆነ በሌሎች የዲጂታል መንገዶች አይገኝም፤ በአካል ብቻ ለሚቀርቡ ይሰጣል።

የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ውጤቱን አሊያም ዲግሪውንና ሌላ ማስረጃውን የሚያወጣ ተገልጋይ የጠፋ ከሆነ ከፖሊስ መምሪያ ማስረጃ ይዞ እንዲመጣና 400 ብር እንዲከፍል ይጠየቃል። ክፍያው በቴሌ ብር አሊያም በሌሎች የዲጂታል አማራጮች አይታሰብም፤ በባንክ ቤት ተሰልፎ ከፍሎ ማስረጃ ማምጣት ግድ ነው። ምክንያቱም ተቋሙ ገና አሠራሩን አላሻሻለም።

ሁሉንም ሂደቶች አልፎ እስከ ረፋዱ 5 ሰዓት ድረስ ፎቶና የሚጠበቅበትን መስፈርት ያሟላ አመልካች፤ በማግስቱ አሊያም በሁለተኛው ቀን ከሰዓት ቀጠሮ ይያዝለታል።

ይሁንና በቀጠሯቸው ቀን በቦታቸው የተገኙ ተገልጋዮች መረጃውን ለመውሰድ ከሰዓት ብቻ ከቀኑ ስምንት ሰዓት ላይ ወደቅጥር ግቢው እንዲገቡ ይፈቀድላቸዋል። ምክንያቱም ትዕዛዝ ነው የሚል መልስ ይሰጣቸዋል።

በጠራራ ጸሐይ መሃል አራት ኪሎ ላይ በቢሮው ደጃፍ የተኮለኮሉ ተገልጋዮችን ማየት በየቀኑ የተለመደ ነው። ሰዓቱ ደርሶ ግቢ የተባሉ ሰዎች በቀጥታ ወደአዳራሹ እንዲሄዱ ይነገራቸዋል። ይሁንና ፈራሚ ባለመኖሩ ብቻ ለዛሬ ማስረጃችሁ አልደረሰም የተባሉ 200 ገደማ ተገልጋዮች በግቢው ቅሬታቸውን ሲያሰሙ ተገኘሁ።

የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ግቢ ውስጥ ከተለያዩ ከተሞች የመጡ፣ በጸጥታ ሥራ ላይ የተሰማሩ ዜጎችን ጨምሮ ሴቶችና የተለያዩ ተቋማት ሠራተኞች “እንዴት ፈራሚ ባለመገኘቱ ብቻ ከየተቋማችን አምጡ የተባልነውን ማስረጃ ማግኘት ሳንችል እንቀራለን” በሚል ቅሬታቸውን አሰምተዋል።

ከአምቦ የመጣው አበራ ሰለሞንና ከአዲስ አበባ ከሥራዋ አስፈቅዳ የመጣችው ሰላማዊት ደስታ ከቅሬታ አቅራቢዎቹ መካከል ናቸው።

በተቀጠርንበት ሰዓት ብንገኝም ወደአንድ ጨለማ አዳራሽ ውስጥ ካስገቡን በኋላ አንድ ሰው ተገኝቶ ይቅርታ ለዛሬ ማስረጃ አታገኙም የሚል የብስጭት መልስ ሰጥቶ አሰናበተን ሲሉ ተናግረዋል።

ለምን ማስረጃችን እንዳልተዘጋጀ ስንጠይቅ ኃላፊዎች በሙሉ አዳማ በመሄዳቸው የሚፈርም ሰው የለም የሚል ምላሽ ማግኘታቸውን ይገልጻሉ።

በተመሳሳይ የጠፋ የትምህርት ማስረጃውን ለመውሰድ ከመቀሌ የመጣው ሀብታሙ ገብረእግዚአብሔር (ስሙ የተቀየረ) በበኩሉ፤ በተቀጠረበት ቀን ማስረጃውን ባለማግኘቱ ለሆቴል ማደሪያና ለምግብ እንዲሁም ለተለያዩ ተጨማሪ ወጪዎች መዳረጉን በምሬት አስረድቷል።

በስተመጨረሻ ከብዙ ጭቅጭቅና እሰጥ አገባ በኋላ በቀጣዩ ቀን ከሰዓት በመሄድ ማስረጃውን መውሰዱን የተናገረው ሀብታሙ፤ የሠራተኞቹ ግልምጫ ከአንድ ተቋም ሠራተኞች የማይጠበቅ ነው ሲል ተናግሯል።

በርካታ ተገልጋዮችም ተቋሙ ምቹ አገልግሎት መስጠት እንዳለበትና ችግሮቹን ወቅቱ መቅረፍ እንዳለበት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በየተቋም የትምህርት ማስረጃ ይጣራ፤ ከ12ኛ ክፍል ውጤት ጀምሮ ማስረጃችሁን አምጡ የሚሉ ጥሪዎች እየቀረቡ ነው። በተለያዩ ምክንያቶች የጠፉ ማስረጃዎች ደግሞ የሚገኙት በትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ተቋም ነው።

ቅሬታውን በተመለከተ ወደኃላፊዎች ቢሮ ብናመራም ከተቋሙ ዋና ኃላፊ አንስቶ ምክትሎች ጨምሮ የተለያዩ ባለሙያዎች ወደአዳማ ለስብሰባ ማምራታቸውን ፀሐፊዎቻቸው አስረዱን።

በተገልጋዮች ማስረጃ ላይ ፊርማቸውን ማኖር ያለባቸው ኃላፊዎች ሲቀሩ በምትካቸው አገልግሎት እንዲሰጡ የተመደቡ ሰዎችም በእረፍት ምክንያት ሥራቸው ላይ አለመሆናቸውን ተረዳን። በስልክ አማካኝነት ምላሽ ለማግኘት ያደረግነው ሙከራም አልተሳካም።

ዜና

# በየሩብ ዓመቱ በሕገወጥ ንግድ ከ106 ሺህ በላይ የቁም እንስሳት ከሀገር ይወጣሉ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ጥናት በተደረገበት የምስራቅ ኢትዮጵያ ብቻ በየሩብ ዓመቱ ከ106 ሺህ በላይ የቁም እንስሳት በሕገወጥ ንግድ ከሀገር እንደሚወጡ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የድንበር ተሻጋሪ ሕገወጥ ንግድ የቁም እንስሳትና ሌሎች የግብር ግብዓቶች ንግድ ላይ ያለውን ተጽዕኖ አስመልክቶ ጥናት ይፋ አድርጓል።

ባለድርሻ አካላት በተገኙበት የጥናት ውጤቱን ይፋ ያደረጉት በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የግብርና ኢኮኖሚክስ ክፍል ከፍተኛ ተመራማሪ ዶክተር ረሂማ ሙሰማ እንደገለጹት፤ ከኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሁሉም አይነት የቁም እንስሳትና የግብርና ውጤቶች በሕገወጥ መንገድ ከሀገር ይወጣሉ።

የጥናቱ ውጤት እንዳመላከተው በየሩብ ዓመቱ ከ106 ሺህ በላይ የቁም እንስሳት በሕገወጥ መንገድ ከሀገር ይወጣሉ ያሉት ዶክተሯ፤ ይህ ለማሳያነት ጥናት በተደረገበት በምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢ ብቻ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የሰሜን፣ የሰሜን ምዕራብንና የደቡብ አካባቢዎች በጥናት ቢካተቱ ከዚህ በላይ የቁም እንስሳት እንደምታጣ የጠቆሙት ተመራማሪዋ፤ በጥናት የተደረሰበት ቁጥር በየዓመቱ ከፍተኛ የቁም ከብቶች ከሀገር እንደሚኮበልሉ ያመላክታል ብለዋል።

እንደ ተመራማሪዋ ማብራሪያ፤ የቁም እንስሳት በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጭ ለመውጣት ብዙ ገፊ ምክንያቶች አሉ። ከነዚህም ውስጥ ወደ መደበኛው ገበያ ለመግባት ያሉ ውጣ ውረዶች መብዛት፤ የአመለካከት ችግር፤ የተሟሉ የንግድ ስርዓትና የገበያ መረጃ አለመኖር ይጠቀሳሉ። የተቀባይ ሀገራትን ፍላጎት የሚያሟላ የተስተካከለ የኳራንታይን ስርዓት አለመኖር እና ያሉት ማዕከላትም አቅማቸው የደከመና አገልግሎት የሚሰጡ አለመሆናቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው።

አርብቶ አደሮች፣ ኢንቨስተሮች፣ የአካባቢው ማህበረሰብ፣ የንግድ ፈቃድ ያላቸው ከትንሽ እስከ ትልቅ ነጋዴዎች በሕገወጥ ንግድ ውስጥ የሚሳተፉ እንዳሉ ጠቁመዋል።

አንዳንድ ጥናቱ በተካሄደባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ኢንቨስተሮች የሚያመርቱትን ምርት ወደ ማዕከላዊ ገበያ ከማቅረብ ይልቅ የቁም እንስሳትን በሕገወጥ ንግድ ወደ ውጭ ያስወጣሉ ብለዋል።

ዘርፉን ሀገራችን ወደ መደበኛ የንግድ ስርዓቱ ብታስገባው ለሀገር ትልቅ ጠቀሜታ አለው ያሉት ተመራማሪዋ፤ ይህ ባለመሆኑ ከፍተኛ የምግብ እጥረትና የውጭ ምንዛሬ ችግር እየተፈጠረ መሆኑን ጠቁመዋል።

የጥናቱ ውጤት እንደሚያመላክተው በተለይ በቁም እንስሳት ዘርፍ እና የግብርና ምርቶች በመደበኛ መንገድ ከሚወጡት ይልቅ በሕገወጥ መንገድ የሚወጡት ይበልጣሉ ሲሉ ገልጸዋል።

ተመራማሪዋ ሕገወጥ ንግዱን ወደ ሕጋዊ መንገድ እመንዲመጣ ማድረግ ይቻላል ሲሉም አብራርተዋል።



ዶክተር ረሂማ ሙሰማ



አቶ አበበ ታደሰ

ከአጎራባች ሀገራት የሰላም ሁኔታ ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ጭምር በመሆኑ በቀላሉ ማስቀረት እንደማይቻል ጠቁመው፤ መደበኛ ንግድን ለማካሄድ ገፊ ምክንቶችን መቀነስና የግንዛቤ ለውጥ እንዲመጣ መስራት ጠቃሚ መሆኑ ጠቅሰዋል።

በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የእንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ የውጭ ንግድ ግብይት ዴስክ ኃላፊ አቶ አበበ ታደሰ በበኩላቸው፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ክትትል ከሚያደርግባቸው የውጭ ንግድ ዘርፎች መካከል አንዱ የቁም እንስሳት ነው።

በየዓመቱ እቅድ በመያዝ የቁም እንስሳትን ወደ ተለያዩ መዳረሻ ሀገሮች በመላክ ከዘርፉ መገኘት ያለበትን ገቢ ለማግኘት ክትትልና ድጋፍ እያደረገ ስለመሆኑ ተቁመዋል።

የቁም እንስሳት ግብይት የሕግ ማዕቀፍ መኖሩን የጠቀሱት ኃላፊው፤ በሕግ ማዕቀፉ መሰረት በሀገር ውስጥ ግብይት እንዲከናወን ድጋፍ የማድረግ፣ ለግብይቱ አመች ሁኔታ እንዲፈጠር የግንዛቤ ፈጠራ ስራ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በመሆን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ፣ በሕገወጥ ንግድ የሚንቀሳቀሱ እንስሳትን የመያዝና ሕጋዊ የግብይት ስርዓትን የማበረታታት ስራ በመስራት ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

# በውጭ ሀገር ለሚኖሩ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በተለይም በኢትዮጵያ ከሚገኙ እኩዮቻቸው ጋር ቁርኝት በመፍጠር የትውልድ ትስስርን ማጠናከር ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በሦስት ዙሮች ወደ ሀገር ቤት እንዲገቡ ጥሪ መቅረቡን ጠቅሰው፤ የእረፍት ጊዜቸውን ተከትሎ ከታህሳስ 20 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ መስከረም ወር 2017 ዓ.ም መጨረሻ ቀናት ድረስ የሚካሄድ መሆኑንም ገልጸዋል።

የመጀመሪያው ዙር ዝግጅት "ከብዝሀ ባህል መሠረቶች ጋር ይገናኙ" (Connect to Culture) በሚል ሃሳብ ከታኅሣሥ 20 እስከ ጥር 30 ቀን 2016 ዓ.ም የተደረገ ጥሪ ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያዊያኑ ወደ ሀገራቸው በመግባት ብዝሃ ባህል የሆነች ሀገራቸውን እንዲያውቁ የሚያስችል ነው ብለዋል፡ ፡

በመርሀ ግብሩ የኢትዮጵያ ሳምንት የተሰኘ ሁነት እንደሚካሄድ አመላክተው፤ የኢትዮጵያ ድምጾችና ጣዕም የተሰኙ ብዝሃነትን የሚገልጹ የተለያዩ ሁነቶችና ጉብኝቶች እንደሚካሄዱ አስታውቀዋል።

ሁለተኛው ዙር ዝግጅት "ታሪካዊ መሠረትዎችን ይወቁ" (Connect to History በሚል ሃሳብ ከየካቲት 20 እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2016 ዓ.ም የሚዘጋጅ መሆኑን ጠቁመው፤ ሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ታሪካቸውን የሚረዱበትና የሚያውቁበት አውድ እንደሚሆን ሃሳብ ሰጥተዋል።

መርሀ ግብሩ የዓድዋ በዓልን ጨምሮ የቀደምት ኢትዮጵያዊያን ታሪክን እንዲያውቁ የሚረዳ መሆኑን ገልጸው፤ በተለይም ኢትዮጵያ ለፓን አፍሪካኒዝም ያበረከተችውን አስተዋጽኦ የሚረዱበት ይሆናል ብለዋል፡፡

ሦስተኛው ዙር ጥሪ ደግሞ "አሻራዎን ያኑሩ የእረፍት ጊዜዎን ያጣጥሙ" በሚል ስያሜ ከሰኔ 10 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ መስከረም 20 ቀን 2017 ዓ.ም የሚቆይ መሆኑን ገልጸው፤ ኢትዮጵያዊያኑ የተጀመሩ ሥራዎችን እንዲያግዙና ለሀገራቸው ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያለመ መሆኑን አስረድተዋል።

ሚኒስትሯ እንዳስታወቁት፤ ለመርሀ ግብሩ መሳካት በቱሪዝም ሚኒስትር የሚመራ ዐብይና ንዑስ ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል።

ጥሪውን ተቀብለው ለሚመጡ የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ሆቴሎች፣ አስጎብኚዎች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

# "በቀጣዮቹ ሦስት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

*ታኅሣሥ አጋማሽ ድረስ በመንግሥትና በአጋር አካላት 15 ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር የሚገመት ድጋፍ እየተዳረሰ መሆኑን ገለጹ።*

ኮሚሽነር ሽፈራው (ዶ/ር) ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳስታወቁት፤ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የፈጠሩትን የሰብአዊ ድጋፍ ፍላጐት በዓመት ሁለት ጊዜ በበልግና በመኸር በሚደረግ አገር-አቀፍ ዳሰሳ ጥናት የሚለይበት አሠራር ተዘርግቷል።

በተጨማሪም የተፈናቃዮችን ሁኔታ የሚከታተልና በየአካባቢው በቅድመ-ማስጠንቀቂያ መረጃዎች የሚደገፍ አሠራርም በዓመቱና በወቅቱ የሚኖረውን የተረጂ መጠን ለመወሰን ጥቅም ላይ ይውላል።

በዚህ አሠራር መሠረት በ2015 በመኸር ጥናት የነበረው የተረጂ ቁጥር 20 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሲሆን፤ በ2015 የበልግ ጥናት ይህ ቁጥር ወደ 15 ነጥብ አራት ሚሊዮን ወርዷል።

በሀገራችን የተካሄደውን 2016 የመኸር ዳሰሳ ጥናት መሠረት በማድረግም በፈረንጆቹ 2024 የሚኖረው የተረጂ ቁጥር 10 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሲሆን፤ በመጀመሪያዎቹ ወራት ማለትም ጥር፣ የካቲትና መጋቢት የሚኖረው የተረጂ ቁጥር ስድስት ነጥብ አራት ሚሊዮን እንደሚሆን ተናግረዋል።

በመሆኑም ከዚሁ ውስጥ በኮሚሽኑ 30 በመቶ እና በክልሎች 70 በመቶ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሹትን በአካባቢው ማኅበረሰብና በልየታ - መስፈርቱ መሠረት ድጋፍ ይደረጋል ብለዋል።

ኮሚሽነር ሽፈራው፣ በድርቅና በጐርፍ ለተጐዱ ወገኖች ከሐምሌ 2015 ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ አጋማሽ ድረስ በሦስት ዙር በመንግሥትና በአጋር አካላት የተላከውን ጨምሮ 15 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር የሚገመት ድጋፍ ለተጎጂው ማኅበረሰብ እየተዳረሰ እንደሚገኝም አመልክተዋል።

እርሳቸው እንደተናገሩት፤ ከ2015 ዓ.ም ከሐምሌ ወር እስከ 2016 ዓ.ም ታኅሣሥ አጋማሽ ድረስ በሦስት ዙር እየተካሄደ ያለው ድጋፍ በኮሚሽኑ አንድ ሚሊዮን 349 ሺህ ኩንታል በ11 ቢሊዮን ብር ወጪ ሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረስ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል። ይህም የመንግሥት ምላሽ በትኩረት እየተከናወነ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው።

በሦስቱም ዙር በመንግሥት እና በአጋር አካላት የተላከውን ጨምሮ አንድ ሚሊዮን 725 ሺህ ኩንታል እየተሠራጨ እንደሚገኝ አስረድተዋል። ይህም የአጋር አካላትን ጨምሮ በብር ሲገመት 15 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር የሚገመት ድጋፍ ለተጎጂው ማኅበረሰብ እየተዳረሰ ይገኛል ብለዋል።

በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች እንደነበሩ የጠቀሱት ኮሚሽነሩ፤ ከእነዚህም መካከል የተረጂነት አስተሳሰብ፣ የተረጂዎችን ቁጥር ማናርና ለአይበገሬነት የሚሆኑ እንቅስቃሴዎችን ከማድረግ ይልቅ ቋሚ ተጧሪ የመሆን ፍላጎት እንደሆኑ ተናግረዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ተገማች ያልሆኑ የአጋር አካላት የሀብት አቀራረብ አሁንም የቀጠለ መሆኑን ጠቁመው፤ በፈረንጆቹ 2023 የቀረበው የሰብዓዊ ድጋፍ ፍላጐት መጠን ሦስት ነጥብ 99 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር መሆኑን ጠቅሰዋል። ይሁንና የቀረበው 33 በመቶ ብቻ እንደነበር አመልክተዋል።

ከዚህ አኳያ አብዛኛውን ሰብዓዊ ድጋፍ መንግሥትና ሕዝብ በራስ አቅም እየተወጣ መሆኑን የሚያመላክት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

# የዓድዋው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ዓድዋ የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ የጋራ የድል ታሪክ ብቻ ሳይሆን፤ የጥቁር ሕዝቦች የሰውነት ማረጋገጫ ማህተም ጭምር ነው። ዓድዋ የጥቁር ሕዝቦች "የሰውነት ታሪክ" መነሻና ጅማሮ በመሆኑ የፕሮጀክቱ ስያሜ የድሉን ፋይዳ በትክክል የሚገልጽ መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል።

ታዲያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሰራቸው ትልልቅ ፕሮጀክቶች መካከል ዓድዋ ዜሮ ዜሮ አንዱ በመሆኑ በቅርቡ የፕሮጀክቱ ግንባታ ተጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት እንደሚሆን የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ጽህፈት ቤትና የካቢኔ ጉዳዮች ኃላፊ አቶ ጥላሁን ወርቁ ይገልጻሉ።

ከለውጡ ወዲህ በመዲናዋ በርካታ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ ተጠናቀው ለአገልግሎት ክፍት ተደርገዋል። በተለይም ሰው ተኮር፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን የሚፈቱ ትልልቅ ፕሮጀክቶች መሠራታቸውን ይገልጻሉ።

በዋናነትም ሰው ተኮር ፕሮጀክቶችን በአጭር ጊዜ በማጠናቀቅ ሕዝብን እፎይ የሚያስብሉ ስኬቶችን ማስመዝገብ ተችሏል።

ሌሎች ላቅ ያለ አንድምታ ያላቸው ፕሮጀክቶችም በግንባታ ላይ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ዓድዋ ሙዚየም የድሉን ታላቅነት የሚመጥን ትልቅ ፕሮጀክት ነው ሲሉም ያስረዳሉ።

የዓድዋ ፕሮጀክት የኢትዮጵያን አሸናፊነት፣ ለጥቁር ሕዝቦችም የድል ምሳሌና የፓን አፍሪካኒዝም መነሻ የሆነ የድል አርማ ነው። በተለይም ለቀጣዩ ትውልድ ግንባታና ለሀገራዊ ትርክት መነሻ እንዲሆን ተደርጎ ተገንብቷል ይላሉ።

ዓድዋ ኢትዮጵያውያን አንድ ስንሆን፣ ስንተባበር ከራሳችን አልፈን ለጥቁር ሕዝቦች ምሳሌ መሆን የሚችል ሥራ መሥራት እንደምንችል የታየበት ነው። ሀገራዊ አንድነትን በማጠናከር የቀደመ ልዕልናችንን ማስከበር እንደሚቻል ለትውልድ እንጠቀምበታለን ሲሉም ይገልጻሉ።

የዓድዋ ሙዚየም ኢትዮጵያን በሚያሰባስብ፣ አንድነትን፣ አሸናፊነትና አይበገሬነትን ለትውልድ ግንባታ ማዋል በሚቻልበት ሁኔታ ለመገንባት የታሪክ ምሁራንን ያሳተፈ መሆኑን ነው የሚገልጹት።

ዓድዋ ፕሮጀክት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሃሳብ አመንጪነት ተጀምሮ በአሁኑ ጊዜ የግንባታ ሥራው 95 በመቶ መጠናቀቁን የሚገልጹት፤ የአዲስ አበባ ትልልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ደቦ ቱንካ ናቸው።

ፕሮጀክቱ ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የተገነባ ሲሆን፤ በውስጡ በዓድዋ ጦርነት የተሰው ጀግኖችን የሚዘክር ሙዚየም፣ መዝናኛ ካፍቴሪያዎች፣ ሲኒማ ቤቶችና ሁለገብ አዳራሾች፣ የሕፃናት መጫወቻ ስፍራን ጨምሮ፣ መኪና ማቆሚያና የንግድ ቤቶችን የያዘ ነው።

እንደ ኢንጂነር ደቦ ገለጻ ከሆነ፤ በፕሮጀክቱ የዓድዋን ድል ተምሳሌትና ሀገራዊ ተጠቃሚነትን በጉልህ የሚያሳይ የ"ፕላዛ" ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

የኢትዮጵያውያንን ታሪካዊና የትርክት አካሄዶችን የሚያሳዩ የጥበብ ሥራዎች የሚሰሩበት በመሆኑ በጦርነቱ የተሳተፉ ኢትዮጵያውንን ታሪክ ማሳየት ይችላል ሲሉ ይገልጻሉ።

ሙዚየሙ በመዲናዋ ከተገነቡና በመገንባት ላይ ከሚገኙ ፕሮጀክቶች ግዙፉ ሲሆን 11 ብሎኮችን የያዘና ሰፊ ቦታ ላይ የተገነባ ነው። በውስጡም የዓድዋ ሰንሰለታማ ተራሮችን፣ የአድዋ ፈረሰኞች ማስታወሻ፣ ለሴት ጀግኖች ክብር የሰጠ ማስታወሻና የአንድነት ማዕከል ያለበት ነው ይላሉ።

ከዚህም በተጨማሪ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት፣ ሁለት ሺህ 500 እስከ አራት ሺህ ሰዎችን ማስተናገድ የሚችሉ አዳራሾች፣ ሲኒማ ቤቶችና አነስተኛ መሰብሰቢያ አዳራሾች፣ የሕፃናት መዝናኛ ስፍራዎች፣ የዓድዋ ድል ማክበሪያ ስፍራ፣ ሞሎችና ሌሎች ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉ ክፍሎችን አካቶ የያዘ ነው።

በአንድ ጊዜ እስከ አንድ ሺህ ተሽከርካሪዎች ማስተናገድ የሚችል ግዙፍ የመኪና ማቆሚያ ስፍራም በውስጡ አካትቷል።

ከሁሉ በላይ ግንባታው አረንጓዴ ስፍራን ታሳቢ በማድረግ የተገነባ በመሆኑ በእያንዳንዱ የፕሮጀክቱ ክፍሎችና በጣሪያው ላይ ጭምር አረንጓዴ ስፍራዎች ይገኛሉ።

ፕሮጀክቱ ከሕንፃው ባሻገር በአካባቢው ያሉትን ስፍራዎችን አካሎ የሚለማ በመሆኑ አካባቢውን ለእይታና ለመኖሪያነት ምቹ ያደርገዋል። ለከተማዋ መሠረታዊ ለውጥም ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው መገንዘብ ይቻላል። ፕሮጀክቱ አዲስ አበባን የመቀየር አንድ አካል በመሆን ትልቅ ለውጥ የሚያስገኝ ይሆናል።

በሌላም በኩል ዓድዋ ፕሮጀክት የአሁኑ ትውልድ ያለውን ታሪካዊ ይዘት ለመጪው ትውልድ ለማስረከብ ያስችላል። ይህም የቀደምት ኢትዮጵያውን ታሪክን ከመዘከር ባሻገር ታሪክን ማጽናት የሚያስችል ነው።

# ወቅታዊ

# "15 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር የሚገመት ሰብዓዊ ርዳታ እየተከፋፈለ ነው"

*- ኮሚሽነር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር)*

*የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር*



አስቴር ኤልያስ

**በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት የሚከሰቱ ፈተናዎችና መፈናቀሎች እየበረከቱ መምጣታቸው የአደባባይ ምስጢር ሆኗል:: ከዚህ የተነሳ ምክንያቱ ምንም ሆነ ምን ከቀዬአቸው የሚፈናቀሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሲቸገሩ ይስተዋላሉ::**

**መንግሥትም ለችግራቸው የሚሆን ጊዜያዊ መፍትሔ ለመስጠት የተቻለውን ሲያደርግ ይታያል:: መንግሥት ከሚያደርገው ድጋፍ በተጓዳኝ ደግሞ ሕዝቡ እርስ በእርስ ሲረዳዳ ማየትም የተለመደ ጉዳይ ነው:: የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 70 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማስተባበርና በማቀናጀት በሀገሪቱ የሚከሰቱ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋን መከላከል፣ መቀነስ፣ ዝግጁነት፣ ምላሽ መስጠት፣ መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ለመተግበር የተመሠረተ ነውና ከዚህ አኳያ ኮሚሽኑ ያከናወናቸው ተግባራትና ተያያዥ ጉዳዮች ዙርያ የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ከኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) ጋር ቆይታ አድርጓል:: መልካም ንባብ::**

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ያከናወናቸው አንኳር ተግባራት ምንድን ናቸው?**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ያቀዳቸው እቅዶች ከ2016 እስከ 2018 የመካከለኛ ዘመን እቅድ ሲሆን፣ በአመዛኙ በ2016 በጀት ዓመት ለሚከናወኑ ቁልፍና አብይ ተግባራት የዝግጅት ምዕራፍ ተደርጎ የሚወሰድ ነው::

የመጀመሪያው ተቋማዊ ለውጥንና አቅም ግንባታን በሚመለከት ሲሆን፣ ከ10 ዓመታት በላይ የቆየውን የአደጋ ስጋት አመራር ፖሊሲን የመከለስ ሥራ ነው:: ዘመኑ የሚጠይቀውን ያልተማከለ፤ በቴክኖሎጂ የተደገፈ፤ በቂና ብቃት ባለው የሰው ኃይል የሚታገዝ ሚዛኑን የጠበቀ የአደጋ ስጋት አመራር እውን ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት አቅርቧል::

ፖሊሲውን ወደ ተግባር ለማሸጋገር የሚያስችል ሥራም ተሠርቷል:: በተለይም ሠብዓዊ ድጋፍን በመንግሥት መሪነት በሀገር-በቀል አቅም ምላሽ የሚሰጥበትን እና ለቅጽበታዊ አደጋዎች ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍና የእሳትና ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች አገልግሎት ለማቋቋም የሚያስችል ደንብ ተዘጋጅቷል:: ይህ ደንብም ለፍትሕ ሚኒስቴር ቀርቧል:: በተቋሙ በፍትሕ ሚኒስቴር በኩልም የመጀመሪያ ግብረ-መልስ በመቅረቡ የማሟላት ሥራ እየተሠራ ይገኛል::

በሌላ በኩል የተቋማችንን መዋቅራዊ አደረጃጀት በኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት እንዲጠና በማድረግና በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ከጸደቀ በኋላ የሰው ኃይል ድልድል በማድረግ ላይ እንገኛለን::

ሌላው በተቋማዊ ለውጥና አቅም ግንባታ ዙሪያ የተከናወነው በመልቲ ሃዛርድ - ኢምፓክት ቤዝድ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ (Multi - Hazard, Impact based Early Warning Early Action Road Map) ፍኖተ ካርታ ላይ በመመስረት ሰፋፊ ዓለም-አቀፍ የግንዛቤ ማስጨበጥና ሀብትን የማፈላለግ ሥራ ተሠርቷል:: በሚቀጥሉት ወራት ወደ ተጨባጭ ተግባራት ለመሸጋገር የሚያስችል ምቹ ሁኔታም ተፈጥሯል::

በዚሁ ሩብ ዓመት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በአራት ቦታዎች ተበታትኖ የነበረውንና በዓመት ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ ለኪራይ የሚከፈለውን ወጪ በማዳን በአንድ ቢሮ የማሰባሰብ ሥራ ተሠርቷል:: ይህም በምልልስ ይጠፋ የነበረውን ጊዜና ሀብት ከማዳኑም በላይ ቀልጣፋና ውጤታማ የአመራር ሥርዓትን ለመተግበር ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል::

ይህንን ምቹ የመሥሪያ ቦታ የተሳለጠ ለማድረግ ባለ ስምንት ወለል ሕንፃ በኮሚሽኑ ቅጥር ጊቢ እያስገነባን ሲሆን፣ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ይጠናቃል ተብሎ ይጠበቃል::

ከተቋማዊ ለውጥና አቅም ግንባታ አኳያ ሌላው በሩብ ዓመቱ በትኩረት የተሠራው ጉዳይ የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት ላልተገባ ዓላማ እንዳይውል በአመለካከት ዙሪያ ከተሰሩ ስራዎች በተጨማሪ የሠብዓዊ ድጋፍ ተጠቃሚዎች የልየታ፣ የምዝገባ እና የቅድሚያ ቅድሚያ የሚያገኙትን የመወሰን አሠራርን መከለስና ከክልሎችና ከአጋር አካላት ጋር መግባባትን መፍጠር ነበር::

በዚሁም የሠብዓዊ ድጋፍ ተረጂ የልየታ ሥራ ተገቢ ካልሆኑ ጣልቃ ገብነት እንዲጠበቅ ተደርጓል:: የሰብዓዊ ድጋፍ ሀብትን ላልተገባ ዓላማ የሚያውሉ በመዋቅርና ከመዋቅር ውጭ ያሉ አካላት ሕጋዊና አስተዳደራዊ ርምጃ እንዲወሰድም ሆኗል:: የዛሬ ተረጂ ቋሚ ተጧሪ እንዳይሆንና የበኩሉን የምርት ድርሻ እንዲያበረክት ድጋፍ ማድረግ፤ የሰብዓዊ ድጋፍ ቁሳቁስ በገበያ፣ በሱቆችና በእህል ወፍጮ-ቤቶች ከተገኘ የሚያስጠይቅ መሆኑ በአሠራሩ ላይ እንዲካተትም ተደርጓል::

**አዲስ ዘመን፡- የአደጋ ስጋትን ስመቀነስ የተሠሩ ሥራዎችስ ምን ይመስላሉ?**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** የአደጋ ስጋትን ለመቀነስ የተሠሩ ሥራዎች ዘንድ ሲመጣ ደግሞ የሀገራችን የአደጋ ስጋት አመራር በአደጋ ስጋት አመራር ምክር ቤት የሚመራ ነው:: ሰብሳቢው የተከበሩ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ናቸው:: ይህ ምክር ቤት መደበኛና ወቅታዊ ስብሰባዎችን በሩብ ዓመት ሁለት ጊዜ ያካሄደ ሲሆን፣ የአስቸኳይ ጊዜ ምላሾችንና ዘላቂ መፍትሔዎችን በማስተባበር ጉልህ ሚና ተጫውቷል::

የአደጋ ስጋትን ከመቀነስ አኳያ ዋናው መሠረት የወረዳ አደጋ ስጋት ፕሮፋይል ሲሆን፣ በሩብ ዓመቱ የተከናወኑትን ጨምሮ 522 ወረዳዎችን መሸፈን ተችሏል:: የአደጋ ስጋቶች አደጋ ፈጥረው ጉዳት እንዳያደርሱ የመከላከል ሥራ የሚፈጸመው የአደጋ ስጋት ፕሮፋይልን መሠረት በማድረግ የመከላከል ሥራ ሲሠራ ነው:: ይህም ከቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃዎች ጋር ተዳምሮ ሴክተሮች የአደጋ ስጋት ቅነሳን በእቅዶቻቸው በማካተት (mainstreaming) እንዲተገብሩ መሠረት የሚጥል ነው::

በሌላ በኩል የወረዳ አደጋ ስጋት ፕሮፋይል መሠረት ያደረጉ ማሳያ ፕሮጀክቶች በአጋር ተቋማት ድጋፍ የተከናወኑ ሲሆን፣ እነዚህም የእንስሳት ርባታ፤ የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ፣ የመስኖ እርሻና መሰል ተግባራትን የሚያካትት ነው::

በዚሁም በአፋር፣ በሶማሌ፣ በኦሮሚያ፣ በሲዳማና በአማራ ክልሎች በአውሮፓ ህብረት፤ በስፓንሽ ድጋፍና በዩ.ኤን.ዲ.ፒ (በUNDP) የተደገፉ ፕሮጀክቶች የዚህ ሩብ አመትን አፈፃፀም ጨምሮ ከ300 ሺ. በላይ ዜጎቻችን ተጠቃሚ አድርገዋል::

የአደጋዎች ምላሽና ማገገምን በተመለከተ እቅድ በተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን ዜጎቻችንን የቅድሚያ ቅድሚያ ድጋፍ የሚፈልጉትን በመለየት ሰብዓዊ ድጋፍ ማድረስን የሚመለከት ነው:: ከዚህ አኳያ ከ2015 ዓ.ም ከመጋቢት ወር ጀምሮ እስከ ታህሳስ አጋማሽ 2016 ዓ.ም ድረስ የአጋር ድርጅቶች ድጋፍ በመቋረጡ መንግሥት በራሱ አቅም የአጋር ድርጅቶች ድርሻንም ጭምር በማካተት ምላሽ ሰጥቷል::

የድርቅ አደጋን በሚመለከት በአማራ ክልል ስምንት ዞኖች፣ በትግራይ ሶስት ዞኖች እና በአፋር ክልል ሶስት ዞኖች እንዲሁም በሌሎች ክልሎችም የተለያዩ ኪስ ቦታዎችን ጨምሮ ሶስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ወገኖች ጉዳት ደርሶባቸዋል::

በሌላ በኩል የጎርፍ አደጋ በሶማሌ ክልል በተለይም ሸበሌ፣ አፍዴርና ሊበን ዞኖች፤ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በተለይም ደቡብ ኦሞ ዞን እና ዳሰነች ወረዳ፤ በኦሮሚያ ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌና ምሥራቅ ባሌ፤ በአማራ ምዕራብ ጎጃም እና ማዕከላዊ ጎንደር፤ በጋምቤላ አኞሐ፣ ኑዌር፣ ኢታንግ ልዩ ወረዳና ጋምቤላ ከተማ፤ በአፋርና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን (1,500,000) በላይ ዜጎች በተለያየ ደረጃ ጉዳት ደርሶባቸዋል:: ከእነዚህ ውስጥ ከ630 ሺ. (630,000) ሕዝብ በላይ ተፈናቅሏል::

በዚህ ጎርፍ ምክንያት 125 ሺ. (125,000) ሄክታር የእርሻ መሬት እና 123 ሺ. (123,000) የግጦሽ መሬት በከፍተኛ ሁኔታ ተጎድቷል:: እስከ 21 ሺ. 500 የሚጠጋ የእንስሳት ሞትን አስከትሏል:: ጎርፉ የወንዝ ፈለጎችን በመጣስ ያደረሰው ጉዳት መንገዶች፣ አገልግሎት መስጫ የትምህርት፣ የጤና እና የውሃ ተቋማት ወድመዋል:: የበሽታ ወረርሽኞችም ያገረሹበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር::

የጎርፍን ሁኔታ ለመታደግ በየክልሉ ምግብና ምግብ-ነክ ያልሆኑ ድጋፎችን እና በውሃ በተከበቡ ደሴቶች ከመከላከያ እና ከባሕር ኃይል በተገኙ ድጋፎች ሕይወት-አድን የሄሊኮፕተርና የጀልባ ኦፕሬሽን በማድረግ ስንቅን የማቀበልና ከአደጋው የመታደግ ሥራዎች ከክልሎች ጋር በመሆን ተከናውኗል:: በተጨማሪም ሰፋፊ የክትባት መርሃ ግብሮችን በማካሄድ ወረርሽኞችን የመቆጣጠር፤ የመጠለያና የውሃ ማከሚያ መድኃኒቶችን በማቅረብ የጉዳት መጠንን የመቀነስ ሰፊ ርብርብ ተደርጓል::

በመንግሥት በኩል እየተደረገ ከሚገኘው ርብርብ በተጨማሪ ለጎርፍ አደጋ ምላሽ የሚሆን ስምንት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በUN-OCHA Central Emergency Response Fund (CERF) በኩል የተገኘ ሲሆን፣ በአጋር ድርጅቶችም በኩል ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል:: በተመሳሳይ በድርቅ ለተጎዱ የሰሜኑ የሀገራችን ክፍሎች 10 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተመደበ ሲሆን፣ ወረርሽኞችንም ለመመከት የሚያስችል አምስት ሚሊዮን ዶላር ተመድቦ በአጋር አካላት በኩል እየተፈጸመ ይገኛል::

በሦስት ዙሮች የተከናወኑ ምግብ፣ ምግብ-ነክ ያልሆኑ የገንዘብ ስርጭቶች የተከናወኑና በመሰራጨት ሂደት ላይ የሚገኙም አሉ:: እነዚህም በድርቅና በጎርፍ ለተጎዱ ወገኖች ከሐምሌ 2015 ዓ.ም ጀምሮ የተከናወነ ተግባር ተጠቃሽ ነው:: በአንደኛ ዙር በሐምሌ እና ነሐሴ ወር የተከናወነው ተግባር 249 ሺ. ኩንታል እና አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በድምሩ ሶስት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር ድጋፍ ለሰባት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ተረጂዎች ነው::

በሁለተኛው ዙር መስከረምና ጥቅምት የተከናወነው ደግሞ 613 ሺ. ኩንታል ለሶስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ተረጂዎች በአራት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ነው:: በሶስተኛው ዙር በመንግሥት 487 ሺ. ኩንታልና በአጋር አካላት 376 ሺ. ኩንታል እንዲሁም 560 ሚሊዮን ብር በድምሩ ለስድስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ተረጂ በመንግሥት አራት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብርና በአጋር አካላት አራት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን በድምሩ ስምንት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን የሚያወጣ ድጋፍ በኅዳርና ታህሳስ ወር እንዲደርስ እየተደረገ ይገኛል::

በነዚህ ሦስት ዙሮች በኮሚሽኑ አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺ. (1,349,000) ኩንታል በ11 ቢሊዮን ብር ወጪ ሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረስ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው:: ይህም የመንግሥት ምላሽ በትኩረት እየተከናወነ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው::

በሦስቱም ዙር በመንግሥትና በአጋር አካላት የተላከውን ጨምሮ አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃያ አምስት ሺ. (1,725,000) ኩንታል እየተሠራጨ ይገኛል:: ይህ በብር ሲገመት በአንድ ላይ የአጋር አካላትን ጨምሮ 15 ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር የሚገመት ድጋፍ ለተጎጂው ማህበረሰብ እየተዳረሰ ይገኛል::

**አዲስ ዘመን፡- በዙሩ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተቀመጠ መፍትሔ ምንድን ነው?**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** በዚህ ሩብ ዓመት ካጋጠሙን

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ወቅታዊ

## “15 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር የሚገመት...

ከገጽ 7 የዞረ



ዋና ዋና ተግዳሮቶች አንዱ የአየር ንብረት ለውጥ ያስከተላቸው ድርቅና ጐርፍ ባለፈው ዓመት ከነበረበት የድርቅ አደጋ ሲያገግሙና በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ደግሞ የግጭት ጫናዎች ለማቅለል በሚሠራበት ወቅት መሆኑ ነው:: ሌላው እስከዛሬ መሻገር ያልተቻለው በአደጋ ስጋት አመራር ሚዛናዊ የሆነ የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ ምላሽና የማገገም ሥራዎች በተገቢው እይታ በመከናወን ዙሪያ የሚታየው የአጋሮችም ይሁን በየደረጃው የሚገኘው የመንግሥት መዋቅር ትኩረት ማሻሻልን የሚሻ መሆኑ ነው:: የአደጋ ስጋቶችን በመከላከል ላይ ያተኮረ ርብርብ ከዜጋው ጀምሮ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ይጠበቃል:: ይህንን የአደጋ ስጋት አመራር ሚዛኑን የጠበቀ የሠብዓዊ ድጋፍ ፍላጐት ሰነድ ላይ በማካተት ዓለም አቀፍ ማህበረሰቡ የተቻለውን ምላሽ እንዲሰጥ በትኩረት ተሠርቷል::

በሌላ በኩል የተረጂነት አስተሳሰብ፣ የተረጂ ቁጥር ማናርና ለአይበገሬነት የሚሆኑ እንቅስቃሴዎችን ከማድረግ ይልቅ ቋሚ ተጧሪ የመሆንና የሠብዓዊ ድጋፍ እንቅስቃሴን በአቋራጭ ባለሀብትነትና ለዘመድ-አዝማድ መጠቀሚያ ለማድረግ የሚሞከሩ ዝንባሌዎች አሉ:: ተገማች ያልሆኑ የአጋር አካላት የሀብት አቀራረብ አሁንም የቀጠለ ሲሆን፣ በፈረንጆች 2023 እንዲቀርብ የተደረገው የሰብዓዊ ድጋፍ ፍላጐት መጠን ሶስት ነጥብ 99 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ነው፤ ይህም በመቶኛ ሲሰላ የቀረበው 33 ብቻ ነበር:: በዚሁም አብዛኛውን ሠብዓዊ ድጋፍ መንግሥትና ሕዝብ በራስ አቅም እየተወጣ መሆኑን የሚያመላክት ነው::

በሩብ ዓመቱ ሌላው ያጋጠመው ተግዳሮት በካፒታል ፕሮጀክቶች አፈጻጸም መጓተት ነበር:: ከነዚህ ከምግብ ማከማቻ መጋዘኖች ግንባታ የተያያዙ ከወሰን ማስከበርና ከዋጋ መናር ችግሮች ሲሆን፣ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን መፍትሔ ለመስጠት ጥረት እየተደረገ ይገኛል::

የአጋር አካላት የሠብዓዊ ድጋፍ ማቋረጥና ከፍተኛ ሀብት መንግሥት እንዲመድብ መደረጉም የሠብዓዊ ድጋፍ በራስ አቅም ለመሸፈን ሰፋፊ የምክክር ሥራ እየተሠሩ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ሀገሪቱ በአሁኑ ወቅት ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች የሚያስፈልግ የምርት መጠን በበቂ ሁኔታ አላት?**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** በሰው ሠራሽ እና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት የሚደርሱ ጉዳቶችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አቅም ለመንግሥት ብቻ የሚተው አይደለም:: በመሆኑም ከማህበረሰብ ጀምሮ በወረዳ፣ በዞን፣ በክልል፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማትና በግል በጐ አድራጊዎች ጭምር አቅም ማሰባሰብ የሚጠይቅ ነው:: በመሆኑ የቅድሚያ ቅድሚያ ድጋፍን በሚመለከት ምላሽ እየተሰጠ ይገኛል::

በሀገራችን በሰፊው እየተተገበረ የሚገኘው የስንዴ ልማትና የሌማት ትሩፋት እንቅስቃሴዎች የኩታ ገጠም የአስተራረስ ዘይቤ ጨምሮ በቂ ምርት እየተመረተ መሆኑ ይታወቃል:: ይሁንና የግብይት ሰንሰለት ቀልጣፋ አለመሆንና የደላላ መረብ የሚፈጥረው መሰናክል የግዥ ዋጋ እንዲያሻቅብ በማድረጉ በተለያዩ በሀገር-ውስጥና በራስ-አቅም አማራጮች ፍላጐታችንን ለመሸፈን እየተረባረብን እንገኛለን::

የሚያስፈልገንን የሠብዓዊ ድጋፍ ፍላጐት በራስ አቅም ለማሟላት የተረጂነት አስተሳሰብ መግራትና ተረጂዎች እንዳይበራከቱ በትጋት መሥራት አንዱ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ተጨማሪ ምርት በማምረት የመጠባበቂያና የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ድጋፍን በራስ አቅም ለማሟላት እየተሠራ ይገኛል::

ይህ እንዳለ ሆኖ መንግሥት በአሁኑ ወቅት የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሹ ወገኖችን አቅምና ሁኔታዎች እስከፈቀዱ ድረስ ለመደገፍና አደጋዎች ወደ ባሰ ጉዳት እንዳይሸጋገሩ ሁሌም ዝግጁ መሆኑን ለማረጋገጥ እንወዳለን::

**አዲስ ዘመን፡- አጋር አካላት የሠብዓዊ ርዳታ ላለመስጠት መፈለጋቸው ይታወቃል:: ለዚህ ዋናው ምክንያት ምንድነው? በአሁኑ ወቅት ያለው የአጋር አካላት ድጋፍስ የሚገለጸው እንዴት ነው?**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** በአሁኑ ወቅት የሚታየው የዓለም-አቀፍ የፖለቲካ አውሎ-ነፋስ ያልተረጋጋና በየጊዜው የሚቀያየር ግለትና ትኩረት የተጫጫነው ነው:: በመሆኑም የሠብዓዊ ርዳታ ከፖለቲካ ፍላጐት ጋር መያያዝ የማይገባው ቢሆንም ነባራዊ ሁኔታው ግን ይህንኑ የሚያሳይ ነው::

በዚሁም ምክንያት በለጋሽነታቸው የሚታወቁ አካላት የሠብዓዊ ድጋፍ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ የመቀነስና ተገማች አለመሆን በስፋት ተስተውሏል:: በተለይም የሠብዓዊ ድጋፍ ፍላጐትን በአደጋ ስጋት አይበገሬነት ለማቅለል የሚገኘው የገንዘብ ድጋፍ ከፍተኛ ማሻሻልን የሚጠይቅ ነው::

በሀገራችን የሚገኙ ለጋሾች የሠብዓዊ ድጋፍ አቅርቦትን ከ2015 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ እስከ መጀመሪያዎች የታህሳስ 2016 ዓ.ም ሳምንታት የገቱበት መነሻ ምክንያት ሠብዓዊ ድጋፍ ላልተገባ ዓላማ ውሏል በሚል ነበር:: ሠብዓዊ ድጋፍን ላልተገባ ዓላማ ማዋል በመንግሥታችንም የተወገዘና የሚያስጠይቅ መሆኑ ቢታወቅም ይህንኑ የተጠያቂነት አካሄድና አዲስ አሠራር በመዘርጋት ሂደት ላይ ልዩነቶች ተፈጥረው ነበር:: በአሁኑ ወቅት በጋራ አሠራር ወደ ሠብዓዊ ድጋፍ አቅርቦት በ20 በመቶ አቅም የተመለሰበት ሁኔታ በጐ ነው፤ በራስ አቅም አመዛኙን ሠብዓዊ ድጋፍ መንግሥትና ሕዝብ እየተሸከመው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል:: ይህም በየትኛው የሠብዓዊ ድጋፍ ሁኔታ (Scenario) ሳይቀለበስ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል::

በዚሁ አጋጣሚ ሠብዓዊ ድጋፍን በሚመለከት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በአጽንኦት መያዝ አለባቸው:: የመጀመሪያው ጉዳይ “ተረጂነት” ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የሚገባበት እንጂ “መደበኛ ሁኔታ“ አለመሆኑን በመገንዘብ በተቻለ ፍጥነት የተለያዩ የልማት አማራጮችን በመጠቀም ከርዳታ መላቀቅን ይጠይቃል:: ለአደጋ ስጋት የማይበገር ሕዝብና ሀገር የመገንባት ራዕያችንን ለአፍታም ቢሆን መዘንጋት የለብንም::

ሁለተኛው ጉዳይ የሠብዓዊ ድጋፍ አቅርቦቶች ዓላማቸው የተጐዱ የህብረተሰብ ክፍሎቻችንን ለመታደግ በመሆኑ የአቋራጭ ባለሀብትነት ፍላጐቶች፣ የዝምድና እና የትውውቅ መጠቀሚያ ማድረግና የሚገባውን መንፈግና የማይገባውን ማካተት የተወገዘና በሕግ የሚያስጠይቅ ጉዳይ ነው:: በዚህ ላይ ሁሉም የፍትህ፣ የፀጥታና የደህነነት መዋቅሮቻችን ርብርብ ይጠይቃል::

ሶስተኛው ጉዳይ በየአካባቢው ማህበረሰብ ይሁንታና በተረጂ ልየታው ጥቅም ላይ በዋሉ ሳይንሳዊ መስፈርቶች የሚለዩ ጊዜያዊ ተረጂዎች አካላዊና አዕምሮአዊ ብቃታቸው እስከፈቀደ ድረስ በወል ልማት ሥራዎች እንዲሳተፉና የአደጋ ስጋት ቅነሳ ድርሻቸውን እንዲያበረክቱ ማድረግ ይገባል:: ይህም የነፃ-ስጦታ አመለካከትን በመቅረፍ በኩል ድርሻ የሚኖረው ሲሆን፣ በወል መሬት ላይ ምርትን መፍጠር ከቻሉ የራሳቸውን የሠብዓዊ ድጋፍ ፍላጐት በራስ አቅም የሚሸፍኑበትን ዕድል የሚያሰፋ ይሆናል::

**አዲስ ዘመን፡- በተያዘው በጀት ዓመት አስቸኳይ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል የሚባሉ ዜጎች ቁጥር ምን ያህል ነው?**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች የፈጠሩትን የሠብዓዊ ድጋፍ ፍላጐት በዓመት ሁለት ጊዜ በበልግና በመኸር በሚደረግ ሀገር-አቀፍ ዳሰሳ ጥናት የሚለይበት አሠራር ተዘርግቷል:: በተጨማሪም የተፈናቃዮችን ሁኔታ የሚከታተልና በየአካባቢው በቅድመ-ማስጠንቀቂያ መረጃዎች የሚደገፍ አሠራርም በዓመቱና በወቅቱ የሚኖረውን የተረጂ መጠን ለመወሰን ጥቅም ላይ ይውላል::

በዚህ አሠራር መሠረት በ2015 በጀት ዓመት በመኸር ጥናት መሠረት የነበረው የተረጂ ቁጥር 20 ነጥብ አንድ ሚሊዮን የነበረ ሲሆን፣ 2015 በጀት ዓመት የበልግ ጥናት ወደ 15 ነጥብ አራት ሚሊዮን ወርዷል:: በሀገራችን የተካሄደውን 2016 የምርት ዘመን የመኸር ዳሰሳ ጥናት መሠረት በማድረግ በፈረንጆቹ 2024 የሚኖረው የተረጂ ቁጥር 10 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሲሆን፣ በመጀመሪያዎቹ ወራት/ወቅት (ጥር፣ የካቲት እና መጋቢት) የሚኖረው የተረጂ ቁጥር ስድስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ይሆናል::

ስለዚህ ከፊታችን በሚገኙ ወራት ሠብዓዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ዜጎች ስድስት ነጥብ አራት ሚሊየን በመሆን ከዚሁ ውስጥ በኮሚሽን 30 በመቶ እና በክልሎች 70 በመቶ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሹትን በአካባቢው ማኅበረሰብና በልየታ - መስፈርቱ መሠረት ድጋፍ ይደረጋል::

እነዚህን ዜጎቻችን ከሠብዓዊ ድጋፍ ጐን ለጐን በተፈጥሮም ይሁን በሰው-ሠራሽ ችግሮች የተጋረጠባቸውን ጉዳት ለመቅረፍ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ እና መዋቅራዊ ድጋፍ በትኩረት የሚሠራ ይሆናል:: የመንግሥትንና የአጋር አካላትን ድጋፍም በተገቢው፣ በተመረጠና ሥነ-ምግባርን በተላበሰ ሁኔታ በመጠቀም “ለወገን ደራሽ ወገን” መሆናችንን የማረጋገጥ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል::

**አዲስ ዘመን፡- ከለጋሽ አካላት ጥገኝነት ለመላቀቅ የሚያስችል ጥናት መዘጋጀቱ ተገልጿል:: ይህ ማለት ድጋፉን በራስ አቅም ለማስኬድ መቻል ነውና በምን አኳኋን ተግባራዊ ለማድረግ ይቻላል? ከአጋር አካላት ውጭ በመንግሥት እንቅስቃሴ ብቻ ርዳታን ማድረስ ይቻል ይሆን?**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** ሠብዓዊ ድጋፍን በመንግሥትና በአጋር አካላት ትብብር መከናወን ዓለም-አቀፍ የሠብዓዊ ድጋፍ መርሆዎችን የሚከተል በመሆኑ እንደ ጉድለት ላይወሰድ ይችላል:: የሠብዓዊ ድጋፍ አቅርቦት በአመዛኙ በአጋር አካላት በሚሆንበት ሁኔታ ግን ፈተናዎች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ ነባራዊ ሁኔታዎች በግልጽ እያሳዩ መጥተዋል::

ከነዚህም መካከል ዕርዳታው የተጠቃሚውን የአኗኗር ዘይቤ ታሳቢ ያላደረገ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በግዥ ትርፍ አምራች ከሆኑት አካባቢዎች አቅርቦቱን ወደ እጥረት ላለባቸው ከማድረስ ይልቅ ከውጭ ሀገር በውድ ዋጋ የሚቀርበው ዕርዳታ የልገሳ ሽፋኑን እየቀነሰው ይገኛል::

በሀገራችን ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች፣ ክረምት-ከበጋ የሚፈሱ ወንዞች፣ ከአጥጋቢ በላይ ዝናብ የሚያገኙ ትርፍ አምራች አካባቢዎች፣ የመስኖ ልማት መሠረተ-ልማት ያላቸው ከግማሽ ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት እና በምርት ተግባር ሊሰማራ የሚችል ወጣት ሕዝብ እያለን ሠብዓዊ ድጋፍን በአመዛኙ በሀገር-በቀል አቅም የማንሸፍንበት በቂ ምክንያት አይኖርም::

በዚሁም በፌዴራልና በክልል ደረጃ የሚያስፈልገንን የመጠባበቂያና የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ደራሽ ርዳታን ከገበያ መሸመት ሳያስፈልግ ተጨማሪ ምርት በማምረት መሸፈን እንደሚቻል ከተደረጉ ዳሰሳ ጥናቶችና ትንተናዎች መረዳት ችለናል:: በተለይም በግብርና የኮሜርሻል ክላስተር አርሶ አደሮች፤ በባለሀብቶችና በበጋ ስንዴ የተገኙ ልምዶች ሠብዓዊ ድጋፍን በአመዛኙ በራስ አቅም በየደረጃው ማሟላት እንደሚቻል ማረጋገጫ ናቸው:: በዚህ ሂደት ሁሉም ባለድርሻዎች ሚናቸውን ከዓለምንም መቆጠብ እንዲያበረክቱ፣ የሀገራችንና የሕዝባችን ክብር ለማስጠበቅ እንዲረባረቡና በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን አብይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደተገለጸው “እውነተኛ ነፃነትን ለመጐናጸፍ እናምርት” መርሆ በአርበኝነት ለማሳካት እየሠራን እንገኛለን::

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፋ ያለ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ::**

**ኮሚሽነር ሽፈራው፡-** እኔም አመሰግናለሁ::

> የተረጂ ቁጥር ማናርና ለአይበገሬነት የሚሆኑ እንቅስቃሴዎችን ከማድረግ ይልቅ ቋሚ ተጧሪ የመሆንና የሠብዓዊ ድጋፍ እንቅስቃሴን በአቋራጭ ባለሀብትነትና ለዘመድ-አዝማድ መጠቀሚያ ለማድረግ የሚሞከሩ ዝንባሌዎች አሉ

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢ በመፍጠር መዋቅራዊ ሽግግርን የማፋጠን ሂደት

**አንተነህ ቸሬ**

መንግሥት መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን እውን ለማድረግ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል ብሎ ትኩረት ከሰጣቸው ተግባራት መካከል የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት አንዱ ነው። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ሦስት ዋና ዋና መሠረታዊ ተልዕኮዎች አላቸው። እነዚህ ተልዕኮዎቻቸው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብ፣ የሥራ እድል ፈጠራን ማስፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማከናወን ናቸው። ፓርኮቹ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች ለሚኖረው የኅብረተሰብ ክፍል የሥራ ዕድል በመፍጠርና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የሥራ ከባቢን እውን በማድረግ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ተመራጭ ከሚያደርጓቸው ነገሮች መካከል በርካታ አገልግሎቶችን በአንድ ሥፍራ ላይ ሰብስበውና አቀናጅተው የሚያቀርቡ መሆናቸው፣ ተገቢ መሠረተ ልማት የሚገነባላቸው እንዲሁም ከሌሎች አምራቾች ጋርም የሚያገናኙ መሆናቸው ይጠቀሳሉ። ከዚህ አንፃር በኢትዮጵያም ብዙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማቋቋም እንዲሁም በአንፃራዊነት በዝቅተኛ ዋጋ የሰውና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን፣ ማሽኖችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባትን፣ የብድር አቅርቦትን፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን እና የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን እንደማበረታቻ በማቅረብ ትልልቅ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ፋብሪካዎቻቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲከፍቱ ጥረቶች ተደርገዋል።

በአሁኑ ወቅት፣ የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣናን ጨምሮ፣ በመላ ሀገሪቱ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ ሲሆን፤ በሥራ እድል ፈጠራ፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ እያበረከቱ ይገኛሉ። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ የአፍሪካ የማምረቻ ዘርፍ መናኸሪያ (Manufacturing Hub) እንድትሆን የሚደረገውን ጥረት ለማቀላጠፍ ላቅ ያለ ሚና ይጫወታል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት በርካታ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች ተገኝተውበታል።

በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚገኙትን የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የሚያስተዳድረው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን እስካሁን የተገኙ ውጤቶችን ለማስፋትና ከኢንቨስተሮች ጋር ያለውን ትስስር ለማሻሻል ካለፈው አንድ ዓመት ወዲህ ልዩ ልዩ የአሠራር ማሻሻያዎችን ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። እነዚህ የሪፎርም ተግባራት ኮርፖሬሽኑ የሀገሪቱን የኢንዱስትሪያላይዜሽን ሂደት ለማፋጠን ለሚያደርገው ጥረት ቁልፍ ግብዓቶች እንደሚሆኑ ታምኖባቸዋል።

ኮርፖሬሽኑ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ሀገሪቱ ከውጭ ንግድ ከአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ እንድታገኝና ከውጭ ይገቡ የነበሩ ምርቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ በማድረግ 750 ሚሊዮን ዶላር ማዳን እንድትችል አድርጓል። በእነዚህ ተግባራቱ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለማቃለል የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል። ከዚህ ባሻገር ከ80 ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል ፈጥሯል፤ ሠራተኞች በተሰማሩባቸው የሥራ መስኮች የአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እውቀትና ክህሎት ባለቤት እንዲሆኑ አድርጓል።

የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ልማት ለማሳደግ ከተደረጉት ጥረቶች መካከል በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተከናወነው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታ ተጠቃሽ መሆኑን ጠቁመው፤ ይህን ጥረት መሠረት በማድረግ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የኢንዱስትሪያላይዜሽን ሂደቱን ለማፋጠን የድርሻውን ሚና እየተወጣ እንደሚገኝ ይገልፃሉ። እሳቸው እንደሚሉት፣ ኮርፖሬሽኑን ለዘመኑ የሚመጥን እና ለኢንቨስተሮች ምቹ የማድረግ ጥረቶች አካል የሆኑት የሪፎርም አጀንዳዎቹ፣ ኢትዮጵያን ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው።

> **ከ ‹‹አጎዋ›› መሰረዝ ጋር ተያይዞ በተፈጠሩ ጫናዎች ምክንያት በ2013 እና 2014 ዓ.ም ብዙ ኩባንያዎች ተጎድተው ከኢትዮጵያ እየወጡ ነበር። በ2015 ዓ.ም እና ዘንድሮ ዓመት ግን አንድም ኩባንያ አልወጣም። ይህ የሆነው የምርት ብዝሐነት እንዲኖር በመደረጉ እና የአውሮፓና የእስያ ገበያዎችን የማፈላለግ ሥራ በመከናወኑ ነው።**

ግልፅ የሆነ የኢንቨስተሮች መመልመያ መስፈርት፣ ቀጥተኛ የዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን / ማስተዋወቂያ/ ዘዴዎች እና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የማበረታቻ ማዕቀፎች ዝግጅት፤ አዲስ የመዋቅር ጥናትና ትግበራ፤ የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ ትብብር መፍጠሪያ እና የዲጂታል አሠራር ሥርዓት ተግባራት ኮርፖሬሽኑ እየተገበራቸው ከሚገኙት የሪፎርም ሥራዎች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

«መንግሥት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ባለሀብቶች አመቺ የኢንቨስትመንት ከባቢ ለመፍጠር ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል። የኢትዮጵያን እምቅ የኢኮኖሚ አቅም ለመጠቀም በኢንዱስትሪ፣ በግብርና፣ በቱሪዝም፣ በማዕድንና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፎች ወሳኝ የማክሮ-ኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳዎችን ይፋ አድርጓል። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የሪፎርም አጀንዳዎችም እነዚህን ሀገራዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን በብቃት የማስፈፀም ዓላማ አላቸው» ይላሉ።

አቶ አክሊሉ፣ ኮርፖሬሽኑ ባከናወናቸው የሪፎርም ተግባራት በርካታ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች መመዝገባቸውን ያስረዳሉ። ኮርፖሬሽኑ የተገበረው የ«ጎልደን ሪሴፕሽን» (Golden Reception) ሥርዓት ባለሀብቶች ከውጭ ሲገቡ በኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ጭምር አቀባበል ተደርጎላቸው በአጭር ጊዜ እንዲስተናገዱ ያስቻለ የአሠራር ሥርዓት ነው። ይህ አሠራር ከዚህ ቀደም ኢንቨስተሮቹ መጥተው ለብዙ ቀናት እንዲቆዩና የቆይታ ጊዜያቸውን እንዲያራዝሙ ለሚያስገድደው የአሠራር ችግር መፍትሄ ሰጥቷል።

የባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ሃሳብ (Proposal) የሚገመገምበት ግልፅ የመመልመያ መስፈርት ተዘጋጅቷል። ኮርፖሬሽኑ የጀመረው «ዜሮ ዌይቲንግ ታይም» (Zero Waiting Time) የአሠራር ሥርዓት፤ የኢንቨስትመንት ሃሳብ በቀረበበት ቀን ተገምግሞ እንዲያልቅ፣ የሚስተካከሉ ነገሮች ከሌሉ፣ ባለሀብቶች ወዲያውኑ ወደ ፓርክ እንዲመሩ፣ ፓርኩን እንዲመለከቱና የቦታ ርክክብ እንዲያደርጉ የሚያስችል ፈጣን የአገልግሎት አሰጣጥ ዘዴ ነው።

ገበያ የማፈላለግና የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ሥራዎችም የሪፎርሙ አካል ናቸው። «ኢንቨስትመንት መምጣት ያለበት ፈልጎን ሳይሆን እኛ ፈልገን ማምጣት አለብን ብለን ለአውሮፓ፣ ለእስያ እና ለአንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት ገበያ ይህን የሚከታተል ልዩ ቡድን አዋቅረን፣ ወደነዚህ አካባቢዎች በመሰማራት ኢንቨስትመንት የምናስተዋውቅበት አሠራር ቀይረናል። ስለዚህ ኢንቨስትመንት የምናመጣው አስተዋውቀንና ጠይቀን እንጂ፣ ባለሀብቱ ወደ እኛ መጥቶ ጠይቆና ጠብቆ አይደለም የሚስተናገደው» በማለት ይገልፃሉ።

ቀደም ሲል በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚመረቱት ምርቶች የ«አጎዋ» (AGOA) ገበያን ታሳቢ ያደረጉ ነበሩ። ይህም ኢትዮጵያ ከ«አጎዋ» ተጠቃሚነት ስትሰረዝ በአምራቾች ላይ ችግሮችን ፈጥሯል። ይህ አሠራር በኮርፖሬሽኑ የሪፎርም ሥራዎች አማካኝነት ተቀይሯል። ከዚህ ቀደም የነበረው የምርት ዓይነት በአብዛኛው፣ «አጎዋ»ን ታሳቢ ያደረገ፣ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ላይ ያተኮረ ነበር። አሁን ግን የፓርኮቹ ምርቶች ዓይነታቸው በዝቶ በግብርና ማቀነባበር (Agro Processing)፣ በማሽነሪና አውቶሞቢል፣ በፋርማሲዩቲካል እና በጨርቃ ጨርቅ ምርት ላይ ያተኮረ እንዲሆን ተደርጓል።

አቶ አክሊሉ እንደሚናገሩት፣ ከ«አጎዋ» መሰረዝ ጋር ተያይዞ በተፈጠሩ ጫናዎች ምክንያት በ2013 እና 2014 ዓ.ም ብዙ ኩባንያዎች ተጎድተው ከኢትዮጵያ እየወጡ ነበር። በ2015 ዓ.ም እና ዘንድሮ ዓመት ግን አንድም ኩባንያ አልወጣም። ይህ የሆነው የምርት ብዝሐነት እንዲኖር በመደረጉ እና የአውሮፓና የእስያ ገበያዎች የማፈላለግ ሥራ በመከናወኑ ነው። ከዚህ ቀደም ኮርፖሬሽኑ ገበያ የማፈላለግ ኃላፊነት አልነበረውም። በሪፎርሙ አማካኝነት ይህን ኃላፊነት እንደ አንድ ክፍተት መሙያ አድርጎ በመውሰድ ኮርፖሬሽኑ ገበያ የማፈላለግ ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል። በ2014 ዓ.ም ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በኢንቨስትመንት ለመሰማራት ጥያቄ ያቀረቡት ባለሀብቶች ከ10 ያልበለጡ ነበሩ። በ2015 ዓ.ም 53 አዳዲስ ባለሀብቶች ገብተዋል።

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ከሚገኙ 177 ሼዶች መካከል አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን እየጠበቁ ያሉት 20ዎቹ ብቻ ናቸው፤ 157 ሼዶች በባለሀብቶች ተይዘዋል። ቀደም ሲል በርካታ ፓርኮች ባዶ ነበሩ፤ አሁን አምስት ፓርኮች (አዳማ፣ ቦሌ ለሚ፣ አዲስ፣ ሰመራ እና ድሬዳዋ (የማኑፋክቸሪንግ ክፍሉ) በመሙላታቸው አዳዲስ ኢንቨስተሮችን ማስተናገድ አይቻልም።

«ከዘጠኝ ወራት በፊት በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ አንድ ኩባንያ ብቻ ነበር። ከሰባት ወራት በፊት ሰመራ ኢንዱስትሪ ፓርክ ምንም ኩባንያ አልነበረውም። አሁን እነዚህ ፓርኮች ውስጥ ውል ፈርመው፣ ክፍያ ከፍለው አንዳንዶቹ ሥራ ጀምረዋል (ለምሳሌ አዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ያሉት ሁሉም ኩባንያዎች ሥራ ጀምረዋል)፤ ሌሎቹ ደግሞ ማሽኖችን በማስገባትና በመትከል ላይ ይገኛሉ። በሪፎርሙ የሠራናቸው ሥራዎች፣ የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት እንዲሁም መንግሥት የሚተገብራቸው የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርም ተግባራት የኢንቨስትመንት ዘርፉ በከፍተኛ ደረጃ እንዲነቃቃ ትልቅ እገዛ አድርገዋል» ሲሉ ጠቅሰዋል።

በተቀናጁ የግብርና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት የተከናወኑ ተግባራት ከአርሶ አደሮች ጋር ያለውን ትስስር በማሻሻል አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን አስችለዋል። ለአብነት ያህል ጅማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ከአቮካዶ ዘይት የሚያመርተው «አክሻይ ጄይ» ኩባንያ (Akshay Jay Oil) ከአካባቢው አርሶ አደሮች ጋር ስምምነት ፈፅሞ ምርታቸውን ይቀበላል። ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የቢራ ብቅል የሚያመርተው «ሱፍሌ ማልት ኢትዮጵያ» ፋብሪካ (Soufflet Malt Ethiopia) ከ70 ሺ በላይ ከሚሆኑ የአርሲና የባሌ አካባቢ አርሶ አደሮች ጋር ትስስር ፈጥሮ እየሠራ ይገኛል። ወደ ደብረ ብርሃን ኢንዱስትሪ ፓርክ የገባው «ቡርትማልት» ኩባንያ (BOORTMALT) ከ50 ሺ በላይ ከሚሆኑ የአካባቢው አርሶ አደሮች ጋር የገበያ ትስስር ፈጥሯል።

ከዚህ ቀደም ከነበሩ ችግሮች አንዱ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የሚሰጠው ቦታ አነስተኛ መሆኑ እንደነበር የሚጠቅሱት አቶ አክሊሉ፣ በ2015 እና 2016 ዓ.ም የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች እንዲነቃቁ ባለሀብቶቹ ያሉባቸውን የፋይናንስና ሌሎች ክፍተቶችን የሚሞሉ ተግባራት እንደተከናወኑ ያስረዳሉ። በመሆኑም በ2015 እና ዘንድሮ ከተመዘገቡት ባለሀብቶች መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ናቸው» ብለዋል።

አንዳንድ ችግሮች ሲፈጠሩ ጓዙን ጠቅልሎ የሚሄድ የውጭ ኢንቨስትመንት ላይ ጥገኛ ሆኖ መቀጠል ተገቢ እንዳልሆነም አስታውቀው፣ ተወዳዳሪ የሆነ የሀገር ውስጥ ባለሀብት ማሳተፍ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት የተጀመረው ሥራ ውጤት እያመጣ ይገኛል ሲሉ አስታውቀዋል። የውጭ ባለሀብቶች ያሉባቸውን ችግሮች በመፍታት ባሉበት እንዲቆዩ ማድረግና እና አዳዲስ ኢንቨስትመንት እንዲመጣ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ሥራዎችን ማጠናከር የሪፎርሙ ማዕከል መሆናቸውንም አመልክተዋል። በአጠቃላይ የሪፎርም አጀንዳዎቹን በብቃት በመተግበር ኢትዮጵያን ከዓለም አቀፍ የኢንዱስትሪ እሴት ሰንሰለት ተገቢውን ድርሻ የምታገኝ ተመራጭ የኢንዱስትሪ መናኸሪያ እንድትሆን ለማስቻል ጥረት እንደሚደረግ አቶ አክሊሉ አመላክተዋል።

# ጎሜ

# እስከ መቼ ብረት እናነሳለን ?

**ምሕረት ሞገስ**

እነተሰማ መንግሥቴ፣ ገብረየስ ገብረማሪያም እና ዘውዴ መታፈሪያ እንደልማዳቸው በማምሻ ግሮሰሪ ተገናኝተዋል:: የዕለቱ ውይይታቸው ኢትዮጵያውያን ጥያቄዎችን እና ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ባህል ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ጠንከር ያለ ቃላት ሲሰናዘሩ ነበር:: ተሰማ ‹‹ኢትዮጵያውያን ሰላም ለማምጣት የሚያግዝ መልካም ባህል አላቸው፤ ይህንንም ሲያሳድጉት ኖረዋል›› ሲል፤ ገብረየስ በበኩሉ ፤ ‹‹ኢትዮጵያውያን ከሰላም ይልቅ እልህ በማብዛት ጦርነትን ያዘወትራሉ ይህ ተግባር አሁንም ሀገሪቱን እየጎዳት ይገኛል::›› የሚል ሃሳብ አቀረበ::

ዘውዴ በበኩሉ፤ ‹‹የኖረ ሰላም ለማምጣት የሚያስችል ሽምግልናን የመሰለ ምርጥ የመወያያ እና ተነጋግሮ ችግር የመፍታት ባህል አለ:: ነገር ግን በሴራ ፖለቲካ ምክንያት ይህ ምርጥ ተነጋግሮ ችግሮችን የመፍታት እና ከግጭት ይልቅ ሰላምን መርጦ ያንን የማስቀጠል ሁኔታ ቆሟል:: ቀድሞም ቢሆን ተማርን በሚሉ ሰዎች አጉል ጥያቄ ምክንያት የማህበረሰብ አስተሳሰብ ተበላሽቷል:: በአጉል የፖለቲካ አስተሳሰብ የመከባበር እሴት በመጥፋቱ፤ ማህበረሰቡ በጦርነት አዙሪት ተበርዟል:: በዚህ ላይ የማህበረሰብ አስተሳሰብ ዕድገት ካልመጣ ለውጥ ማስመዝገብ እና ከግጭት እንዲሁም ከጦርነት መውጣት አይቻልም:: ነገር ግን ኢትጵያውያን ከግጭት እና ከጦርነት ይልቅ ሰላም የሚያሰፍን ባህል አለን::›› ሲል ተናገረ::

ገብረየስ በበኩሉ፤ ‹‹በእርግጥ እውነት ኢትዮጵያውያን በእልህ ብረት ከማንሳት የወጣ በመነጋገር የሚያምን ባህል ካለን ያ ባህል የት ገባ ? ብለን መጠየቅ አለብን:: እኔ በዘመኔ የተረዳሁት ኢትዮጵያውያን እልኸኞች እና በጦርነት የምናምን ሰዎች መሆናችንን ነው:: በእርግጥ እኔም የጦርነት ተሳታፊ ሆኜ በሂደቱ አልፌያለሁ:: የጦርነትን አስከፊነት በደንብ መግለፅ እችላለሁ:: ምክንያቱም በአካል ተሳትፌ ምን ያህል ጎጂ እንደሆነ አረጋግጫለሁ:: ጦርነት ጉዳቱ እንዲህ በቀላሉ ተገልፆ የሚያልቅ አይደለም::

በጦርነት ያለፈ ሰው የቅርብ ጓደኛው ሲሰዋ አይኑ ስለሚያይ እና ሌሎችም ሰዎች ሲሞቱ እና አካላቸው ሲጎድል ስለሚመለከት፤ እንዲሁም እርሱም እሞታለሁ ብሎ ሲያስብ በተለያዩ አጋጣሚዎች በመትረፉ እስከሚሞትበት ቀን ድረስ ሕሊናው ስለጦርነት ከማሰብ ወደ በኋላ አይልም:: እስከ ሕይወቱ ፍፃሜ ያ ቁስል ሲያመው፣ ሲያደማው እና ሲከተለው ይኖራል:: ጠባሳው እስከ ትውልድ የሚተላለፍ ነው::

በእርግጥ አሁን ይህ ኢትዮጵያ ላይ የማያቋርጥ ልማድ ሆኗል:: ልማዱ የመጣው ገዳይ እንደጀግና ስለሚቆጠር እና ባህላችንም በገዳይነት የሚያምን በመሆኑ ነው:: እንኳን ገዳይነት ማንኛውም አንድ ነገር ከተለመደ በኋላ ነገሩን ለማቋረጥ ስለሚከብድ ከጦርነት ይልቅ ሰላማዊ አማራጮችን ማየት ያዳግታል:: በእኔ እምነት ኢትዮጵያውያን ልዩነትን ለመፍታት ከምንመርጠው አማራጭ ውስጥ ዋነኛው እና የምንወድው ጦርነትን ነው:: ይሔ ደግሞ በምንም መልኩ አዋጭ አይደለም:: ሕዝብ አልቋል:: ንብረት ወድሟል:: እልሃችን ሀገርን ወደ ፊት እንዳትራመድ እግሯን እየጎተተ አላላውስ ብሏታል:: በዚህ ላይ መተማመን ይገባል::›› ሲል ገብረየስ የሚያስበውን ተናገረ::

ዘውዱ ደግሞ፤ ‹‹በእኔ እምነት ኢትዮጵያውያን ሁል ጊዜም የሚመርጡት ጦርነት ነው በሚለው ሃሳብ አልስማማም:: ዋነኛው ችግር ሌላ ነው:: ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው እንደሚባለው አንድ ሰው በአንድ ምክንያት ተጎዳሁ ብሎ ሲከፋ እና ሲበሳጭ በምክር ለመታገስ መሞከር እና ጥያቄውን መመለስ እንጂ መጥፎ ነገር እንዲሠራ መገፋፋት ተገቢ አይደለም:: እኔ ግጭት ለመከሰቱ ዋነኛው ችግር ማህበረሰቡ ጥያቄ ሲያቀርብ ከመታገስ እና ተገቢውን ምላሽ ከመስጠት ይልቅ አንዳንዴ ችግርን ላለማየት አይንን የመጨፈን ያህል ጥያቄን ያለመመለስ ክፍተት በመኖሩ ነው የሚል እምነት አለኝ::

ለማየት የፈለገ አይኑን ይገልጣል፤ ፍላጎት ካለ የሚፈልገውን ተግባር ማከናወን ይቻላል:: ነገር ግን አንድ ማህበረሰብ የሚፈልገውን ጥያቄ ሲያቀርብ መልስ አለመስጠት ማህበረሰቡ የሃይል አማራጭ ውስጥ እንዲገባ መገፋፋት ነው:: በእኔ እምነት የሕዝቡ ባህል ግጭት ወዳድነት ላይ የተለጠፈ ሳይሆን ምላሽ ባለማግኘቱ ግጭት እየተፈጠረ ነው የሚል እምነት አለኝ:: » ሲል ተናገረ::

ተሰማ ዘውዴንም ገብረየስንም ሳይቃወም፤ መሃል ላይ መሆኑን በሚያሳውቅ መልኩ ‹‹ጦርነት እና ግጭት የኢትዮጵያውያን መገለጫ ስለመሆኑ መካድ ለእኔ ከባድ ነው:: ኢትዮጵያ በተለይ ከ1960ዎቹ ጀምሮ በእርስበእርስ ጦርነት እና ግጭት ስትታመስ ቆይታለች:: ይህ ዘውዴ እንደገለፀው የማህበረሰብን ጥያቄን ከመመለስ እና ካለመመለስ ጋር ብቻ የተያያዘ አይመስለኝም:: ምክንያቱም ከእርስ በእርስ ባሻገር ጦረኞች መሆናችንን ጥንት ከድርቡሽ ጋር፣ ከጣሊያን እና ከሶማሌ ጋር ባካሔድነው ጦርነት ላይ አስመስክረናል:: ያለፉትም ሆኑ ያለው መንግሥታት የማህበረሰብ ጥያቄዎችን ለመፍታት ጥረት አድርገዋል፤ ጥረትም እያደረጉ ነው::

ነገር ግን ሆድ እና ጀርባ ከመሆን መዳን አልተቻለም:: በክልሎች ውስጥ አንዳንዴም በክልሎች መካከል የሚደረግ ግጭትን ከሥሩ ለመንቀል አዳጋች ያደረገው ጥያቄዎች ባለመመለሳቸው አይመስለኝም:: እኔ እንደማምነው ጦርነትን ባህላችን በማድረጋችን ይመስለኛል::›› ሲል ተሰማም ያሰበውን ተናገረ::

ዘውዴ ተቆጣ፤ ‹‹ይህማ ትክክል አይደለም:: እንዴት ሰው ጦርነትን ባህል አድርጎ ዘላለሙን ሲዋጋ ይኖራል ? ለእኔ ከ1960ዎቹ ጀምሮ ሀገር ውስጥ ለሚፈጠሩ ጦርነቶችም ሆነ ግጭቶች መነሻው የፖለቲካ ሴራ ነው:: የሴራው ተሳታፊዎች እና የጦርነት ወይም የግጭት ደጋፊዎች የአንዱ መነካት ለሌላው መጎዳት ምክንያት እንደሚሆን የማወቅ ክፍተት ነበረባቸው::

ሰዎቹ ሃረጉን ሲስቡት ዛፉ ይወዛወዛል እንደሚባል ረስተዋል:: በየትኛውም መልኩ አንዱ ሲነካ ሌላው መጎዳቱ የማይቀር መሆኑን ዘንግተዋል:: በእርግጥ አሁን ላይ ግጭት አለ:: አሁን ያለው ያለፈው ውላጅ ነው:: አሁን ያለውን ግጭት ለማስቆምም ሆነ ችግሩን ከስሩ ለመንቀል፤ ለሚያስማማ እና ለሚያከባብር ጉዳይ ቅድሚያ መስጠት በዚህም ሁሉንም ወደ አንድ መንፈስ በመሳብ ውጤት ማምጣት ይቻላል:: ከዚህ ውጪ ጦርነት ባህላችን ነው ብሎ በማህበረሰብ ጥያቄ ላይ ማሾፍ ጭራሽ የማይገባ እኛን ከመሰለ ትልልቅ ሰዎች ፍፁም የማይጠበቅ ነው::›› ሲል በቁጣ ተናገረ::

ተሰማ፤ ‹‹መቆጣትም አይገባም:: ሃሳባችንን እየገለፅን ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ ጦርነት እና ግጭት እንደባህል እየታየ እየቀጠለ ያለ ጉዳይ ነው የሚል ሃሳብ በማቅረባችን ትክክል ካልሆንን በሃሳብ ልታሳምነን ይገባል:: ቁጣም ከጦርነት ወይም በሃይል ለማሳመን ወይም በሃይል ለመግዛት ከመሞከር የተለየ አይደለም::

‹ጥንት መከባበር ነበር:: መከባበር በመኖሩ ጦርነት አልነበረም:: የአሁኑ ችግር መከባበር በመጥፋቱ የተፈጠረ ነው::› ካልክ በደንብ ማሳያ አቅርብና እንተማመን:: ከዚህ ውጪ ግን ማንም ቢሆን ድልድይ ከሌለ ወንዝ መሻገር ሲያምረው ይዋኛል፤ ሊሞግት ያማረው ይዳኛል እንደሚባለው ነው:: አንድን ጉዳይ ለመፈፀም የሚፈልግ፤ ያሻውን ለማግኘት ይሠራል:: አሁን እንዳየነው መጋጨት የሚፈልግ በግጭት ውስጥ እየዋኘ ይቆያል:: ነገር ግን ሰላም የሚፈልግ ደግሞ ሰላም እንዲመጣ ብረቱን ጥሎ ራሱን ለውይይት ያዘጋጃል::›› ሲል የራሱን ሃሳብ ገለፀ::

‹‹ግጭት በየትኛውም ዓለም የነበረ፣ ያለ እና የሚኖር ተፈጥሯዊ ክስተት መሆኑ ይታወቃል:: ነገር ግን ኢትዮጵያ በምንም መልኩ ከግጭት አዙሪት ወጥታ ሙሉ ለሙሉ ፊቷን ወደ ልማት አዙራ የሠራችበት ጊዜ የለም:: ለዚህ ዋነኛው ምክንያት በእኔ እምነት ፖለቲካው ለዜጎች ተገቢውን ምላሽ ባለመስጠቱ ነው::›› የሚል እምነት አለኝ ሲል ዘውዴ ሃሳቡን ለማጠናከር ሞከረ::

ገብረየስ በበኩሉ፤ ‹‹ግን ደግሞ መታየት ያለበት ነገር አለ:: ሁሉም ጦርነት እና ግጭት መነሻው ተገቢ ጥያቄ ነው:: ብሎ መደምደም አይቻልም:: ሁሉም ጥያቄ መመለስ አይችልም:: ለምሳሌ የፕሬዚዳንትነት ጥያቄ ቢነሳ ፕሬዚዳንት መሆን የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ነው:: ከእዛ ውጪ 150 ሺህ ሰው የፕሬዚዳንትነት ጥያቄ ቢኖረው ሁሉም ያሻውን ሊሰጠው አይችልም:: ለአንዱ ሲሰጥ ለሌላው መከልከል የግድ ነው:: በሌላ በኩል ይህ ሁሉ ቢሆንም በሆደ ሰፊነት ለሁሉም በተደጋጋሚ የሰላም ጥሪ እየቀረበ ነው:: ነገር ግን ምላሽ በመስጠት በኩል መዘግየት አለ:: ኢትዮጵያውያን ጦርነትን እንደልማድ ተያይዘነዋል የምንለው ለዚሁ ነው::›› ሲል ተናገረ::

ዘውዴ፤ ‹‹በመንግሥት በኩል ረጅም መንገድ ሄዶ ለሰላም ጥሪ ማቅረቡ ተገቢ ነው:: ነገር ግን በውይይት ሂደት በሌላ ወገን ያለው ብቻ እሺ እንዲል ከመጠበቅ ይልቅ የራስንም ሚና መወጣት ያስፈልጋል:: ለእዚህ ዋነኛው መፍትሔ ሰጥቶ መቀበል ነው:: በእርግጥ ሰዎች ማሰብ ይችላሉ:: ሁሉም ፕሬዚዳንት እንሁን ብለው አይጠይቁም:: ቢጠይቁ እንኳ እንደማይቻል ከተነገራቸው እና በዛም ላይ እንዲያምኑ ከተደረገ ሰላም ማምጣት ይቻላል:: በሌላ በኩል መሳሪያ ይዘው ጫካ የገቡ ማንኛውም አካላት የሰላም አማራጭን በአንደኝነት ማስቀመጥ አለባቸው:: በዚህ ጉዳይ ላይ ካፈርኩ አይመልሰኝ የሚመስል ፈሊጥ አያዋጣም:: በዚህ ምክንያት የሚሞተው ሰው ነው:: ሀገር የሚወድ ለሰው ያስባል::

እኔ ኢትዮጵያውያን ጦርነትን እንደባህል ይቆጥሩታል፤ ይወዱታል መባሉን አልደግፍም:: ምክንያቱም ማንም ሰው ወዳጁ የሀገሩ ሰው እንዲሞት አይወድም:: ቢገፋበት እንጂ ማንም ቢሆን ጦርነትን እንደባህል አይለማመደውም:: አንደኛ ምርጫው አድርጎ አያስቀምጠውም:: ይህንን ልብ ማለት ይገባችኋል›› ሲል መከፋቱን በሚያሳብቅ መልኩ ተናገረ::

ገብረየስ፤ ‹‹የሚያሳምነን ማመን የማያሳምነን መተው የሁላችንም መብት ነው:: የሚዘፈነው ለገዳይ ነው:: ሰላም ላሰፈነ ሲዘፈን አናውቅም:: ገዳይ ግን ይሞገሳል:: ይህንን እውነት መካድ አይገባም:: ዋናው ጉዳይ ይህ ከሆነ በምን መንገድ ዜጎች ለሰላም ቅድሚያ የሚሰጡበትን ሁኔታ እናመቻች፤ በሚለው ላይ ብንነጋገር ይሻላል::

ችግሩን ለማቃለል መጀመሪያ ችግሩ መኖሩን ፤ ችግሩ በምን ያህል መጠን ሥር እንደሰደደ ማወቅ ያስፈልጋል:: ብዙ የጦርነት ታሪኮች አሉን:: ይህንን በታሪክነት ትተን ባህላችንን በተቃራኒው ባለን የሰላም መንገድ ላይ መመስረት አለብን:: በእርግጥም ሰላም ማስፈን የሚያስችሉ በየባህሉ የሽምግልና ባህሎች አሉን:: ይህንን ባህል እንጠቀምበት::›› ሲል ሃሳቡን ሲያስተላልፍ፤ ተሰማ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ በመጨበጥ በሃሳቡ እንደሚስማማ ገልፆ የጠጡበትን ለመክፈል እጁን ወደ ኪሱ ሰደደ::

> ሰላም ላሰፈነ ሲዘፈን አናውቅም። ገዳይ ግን ይሞገሳል። ይህንን እውነት መካድ አይገባም። ዋናው ጉዳይ ይህ ከሆነ በምን መንገድ ዜጎች ለሰላም ቅድሚያ የሚሰጡበትን ሁኔታ እናመቻች፤ በሚለው ላይ ብንነጋገር ይሻላል።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ከአደፍርስ ጥላ ሥር

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ነገር ከዓይን ይገባል፤ እውነት ግን ከልብ ነው... እውቀትን ሰፍረው ሰጡንና ብዙ ያወቅን እየመሰለን የምናውቀው ግን ጥቂት መሆኑ ነው። ይህን እንዳስብ ያደረገኝ አደፍርስ ነበር። ያኔ ገና ትውውቃችን ከመጀመሩ አስቀድሞ ዳኛቸው እያሞካሸ ያወራለትንና ከአዲስ አበባ ወጥቶ በገበሬ ማህበር ውስጥ የተቀመጠውን አደፍርስን ለማየት ጓጓሁና እኔም ተከትዬ ለመሄድ ወሰንኩ። ልቤ ቀደመ ማለት ነው...ካለበት ደርሼ ዓይኔን ሳማትር ከአንዱ ዋርካ ስር ገበሬውን ሰብስቦ ተመለከትኩ።

ሲያዩት ለዓይን የማይሞላ፤ ገበሬ ያውም የገበሬ አምባሳደር እንጂ ሀገርና ሕዝብን በብዕር የተሸከመ ሊቀ ሊህቃን አይመስልም። ብቻ ግን ከስሩ ለተሰበሰቡት ገበሬዎች ምኑን እንደሆን እየቀዳ ያንዠቀዥቅላቸዋል፤ እነርሱም አፋቸውን ከፍተው ይሄን የነገር ውሃ የሚጠጡት እንጂ በተመስጦ እያደመጡት ብቻ አይመስሉም። የወሬ ሱስ አይደለም፤ የሚነግራቸውን ለማድመጥ ቋመጥኩና በቶሎ መጽሐፉን ገለጥኩት። አደፍርስ... ዳኛቸው ወርቁ የዓይን ሳይሆን የልብ እንቁ መጽሐፍ ነው። ስለመኖር ሳይሆን መኖርን፤ ስለሀገር ሳይሆን ሀገርን ያሳየናል።

እየወደድን ባናነበው እንኳን አንብበን መውደዳችን ግን የማይቀር ነው። ዳኛቸውም አደፍርስም፤ ሁለቱም እንዲህ ያሉ ናቸው። ሲያዩዋቸው የማይመስሉ ሲገልጧቸው በሀገር የሚመሰሉ ናቸው። በብዙ ጥራዝ በተጠገጠጉት በእያንዳንዱ የመጽሐፉ ገጾች ውስጥ የምናውቃቸው የመሰሉን፤ ግን የማናውቃቸው ደብዛዛ መሳይ የእውቀትና የጥበብ ወጋገን እንደዋዛ ይንቦገቦግባቸዋል።

ዳኛቸው ወርቁ፤ እንዲህ ለተመለከተው ሁሉ መልኩ እንደ 'አብስትራክት' ስዕል እየተለዋወጠ ምሁራኑን ሳይቀር በጎራ ለይቶ በሙግት ለማፋጀት ያበቃውን፤ እንዲህ ያለ ጠብሰቅ ያለ መጽሐፍ ለመጻፍ እንዴት ተቻለው? ብዬ እራሴን ጠየኽሁና...ከብዙ የምናብ ድክርቴ መሃል ያገኘሁት አንድ ነገር ቢኖር ደራሲው ለጥበብ የቆመ አብዮተኛ፤ እንዲሁም በዘመኑ ማንም ልብ ብሎ ያላጤነው አንድ ግዙፍ ጽንሰ ሃሳብ የተሸከመ ስለመሆኑ ነው። አደፍርስ የዋዛ መጽሐፍ ብቻ አይደለም።

የአደፍርስ ጽንሰ ሃሳብ ላልገባው ሰው፤ በቃ ምኑም የማይገባ ድፍን ስሜት ነው። ወዲያ ቢሉት ወዲህ ፍንክች አይልም። ለዚህም ነው ጥቂት የማይባሉ አንባቢያን "አሁን ይሄ ምኑ የሚሞገስ መጽሐፍ ነው? ያለ ቂቤ እንደበሰለ ቋንጣ ችክ ብሎ ከጣዕም አልባነቱም ለጥርስ የማይታኘክ ችኮ ነው" በማለት ይህን ያህል ስለመወደዱ ግርምትን ያጭርባቸዋል። የአደፍርስ ሕብለ ሠረሠር የሚገኘው በዓይን አልፈው ከሚገቡት ፊደላት ላይ አለመሆኑ ነው። ከፊደላቱ ምስል የሚወጣው ብናኝ፤ ላልገባው ዓይን የሚያጠፉ አቧራ፤ ለገባው ልብን የሚያበሩ የብርሃን ጨረር ናቸው።

አደፍርስ የዚህ መጽሐፍን የታሪክ ወርቅና አልማዝ የተሸከመና ሠረገላውን ይዞ የሚወነጨፍ መንኩራኩር ነው። ዳኛቸው ወርቁ ከሁሉ መርጦ የዋና ገጸ ባህሪውን ማህተብ፤ የሃሳቡን ኪታብ ከአንገቱ አስሮለታል። አደፍርስ እራሱን መጽሐፉን የመሰለ ለዓይን የማይሞላ የልብ አውቃ ልብ አድርስ ነው። ከወዲያ ቆሞ ከተመለከተው ይልቅ ወዲህ ቀርቦ ላደመጠው ድንቅ ወጣትነቱ ይገለጣል። የ 24 ዓመቱ አደፍርስ ሰበብ፤ መዘዝ የማያጣው ነውና የርሱ መዘዝ በምናብ ለወለደው ዳኛቸውም መትረፉ አልቀረም ነበር። አደፍርስ እንደ ስሙም አደፍርስ ነው።

ስምን መልአክ ያወጣዋል፤ ዳኛቸውም እንደ መልአክ ሆነ። መጽሐፉ ለሕትመት ከበቃ በኋላ ብዙዎቹን አስኮርፏል፤ አለቆቹንም አስቆጥቷል። 'አይ አደፍርስ... የስራህን ይስጥህ' ሲል፤ በ1966ዓ.ም የነበረበትን የሥራ ገበታ ጥሎ ለመሄድ ተገዷል። ዳኛቸው፤ አደፍርስን እንዲህ ነበር የገለጸው፤ "... አደፍርስ፣ ፊተ ሰልካካው ባለሃያአራት ዓመቱ ወጣትን፤ ነገርተኛ ቀርቦ ሲከብበው እና ሲያደምጠው ደስ እያለው ምክር በተለይ በመስጠት ያስተናግዳቸው አለ.... ደብረሲና አደፍርስ ትንሽ ከርሞ በመቀጠል ወደ አጎቱ ችሎት ወረደ።

ብዙዎች የዋና ዳኛው እህት ልጅ በማለት ለምልጃ ይቀርቡት ጀመር። ዳኑ፤ ከማማከር እና ማውራት በቀረ ብዙ ማማለዱን አይከውንም ነበር" አደፍርስ መቼቱ የታነጸው በሰሜን ሸዋ ከደብረ ሲና ተራሮች አናትና




እምብርት ላይ ነው።

ዳኛቸው የተወለደባት፤ እትብቱ የተቀበረባት ሥፍራ ናት። በአደፍርስ ገና ሲጀምር እንዲህ በማለት ይቀድሰዋል፤ "በሰሜን ሸዋ ዞን፤ ይፋት እና ጥሙጋ አካባቢ ኑሮው፤ ከሌላ ሞቅ ያሉ መኖሪያዎች በተለየ፤ እጅግ ቅዝቅዝ ብሎ በህመም ላይ እሚገኝ ነው።

መልከዐምድሩ በከባዱ አስቸጋሪ ሆኖ፤ አኗኗር እጅግ አርብቶ እና አርሶ አደርነት የሞላው እና ከእጅ ወደአፍ እንደሆነ የቀረ፤ በሃይማኖት እና ታሪክ ሥነሥርዓት እና ሂደት የተተበተበ፤ በጠቅላላው እጅግ አስቸጋሪ፣ ያንቀላፋ እና የታመመ ሕይወት ነው" ታሪኩ ሲቀጥልም አደፍርስ ለሥራ ተመድቦ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአዲስ አበባ በመውጣት ወደዚህ ይሄዳል።

አካባቢውን ከመልመድ ጀምሮ ኖሮ ቤተኛ እስከሚሆንበት ድረስ የገጠመውንና የሚገጥመውን ሁሉ በአስደናቂ የቋንቋ ፍልስፍና ጠፍጥፎ ሞልሙሎታል። አደፍርስ ሙልሙልም ድንጋይም ነው። ያወቀበት በልቶ ረሃብን ያስታግስበታል፤ ያልገባው አድርቆ ይፈናከትበታል። ብዙዎች "አወዛጋቢው ደራሲ.... አወዛጋቢው መጽሐፍ" እያሉ የሚገልጹትም ለዚሁ ነው።

አደፍርስ ልቦለዳዊ ዘውግን የተከናነበ እንዲሁም ደግሞ ቁመናና መልኩ ሁሉ በልብወለድ ልኬት የተሰፋ ቢሆንም፤ ከሌሎች የልብወለድ ሥራዎች አንጻር ስንመለከተው ግን ወጣ ያለ ሌላ ባህሪም ጭምር የተላበሰ ስለመሆኑ እንገነዘባለን። በ1962ዓ.ም ታትሞ ለንባብ የበቃው ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ የዘመናዊ የሥነ ጽሁፉ ታሪክ የመጀመሪያው እንደሆነ ይነገርለታል። ከዚያ አስቀድሞ የዘመናዊ ሥነ ጽሁፍን የመግቢያ በር የደረሰበት ጸሐፊ እምብዛም አይታወቅም።

ታትሞ የወጣም መጽሐፍ ባለመኖሩ ዳኛቸው፤ የማንን ፈለግ ተከተሎ አገኘው ቢባል፤ ምናልባትም ምላሹ ሊሆን የሚችለው...የራሱን ነው የሚል ነው። ይህ ጥያቄ ለራሱ ለዳኛቸው ቢቀርብለት ኖሮ "የራሴን ጥላ ምናባዊ ዱካ ተከትዬ ስሄድ ወስዶ ከአንዱ ጋር አደረሰኝና ከዚህ ነው ሲል ልቡስጥላዬ አመለከተኝ" በማለት የሚመልሰው ይመስለኛል። ባይሆን እርሱን ተከትለው ወደ ዘመነኛው የሥነ ጽሁፍ መንደር የገቡ ብዙ ናቸው። የልቦለድ መሳጭነቱ ከልብ አንጠልጣይነቱ ላይ መሆኑን የውጭም ሆነ የሀገር ውስጥ መጽሐፍት ይነግሩናል። እኛም ይህቼን አብዝተን እንወዳታለን። አድፍርስ ግን ይህችንም ልማድ ሳያደፈርሳት አልቀረም።

ልብን እያንጠለጠሉ በስሜት ባህር ከመድፈቅ ይልቅ ጭንቅላትን እየሰቀሉ በእውቀት ውቅያኖስ ውስጥ መድፈቅን ይመርጣሉ። በአንዲት የታሪክ ሴራ ውስጥ ውሎ እያደረ አጀብ አያስነሳም። በዚህም ምክንያት ምንም አይነት ድግግሞሽ አይታይበትም።

ቋንቋ ጸሀፊው እፍ..ብሎ ነብስን የሚዘራበት የሥነ ጽሁፍ እስትንፋስ ነው። ከአዕምሮ እየፈለቀ በጠብታ የብዕርን ጓዳ የሚሞላ እንቁ ሀብት ነው። በአደፍርስ ግን ከምንጩ ተኝቶ የዋኘበት ይመስላል። ለአፍላና ትኩስ አንባቢማ 'ይህ መጽሐፍ ግን አማርኛ ነውን? ወይንስ አማርኛን አላውቅም ኖሯል?' እያስባለ እራሱን ማስረሳቱ የማይቀር ነው።

ደህና ይወስድ ይወስደንና ደግሞ እንደገና ምኑም ከማይገባን ግዙፍ የሾላ ዋርካ ስር አስቀምጦን እብስ ይላል። ተቀምጦ አዙሪቱ፤ ልብን ውርድ ሲያደርግ 'ኤጭ ወዲያ! አሁንስ በዛ' የሚያስብል ቢሆንም፤ ቅሉ ታግሶ ዙሪያ ገባውን ተመልክቶ ለታገሰ ከሾላዋ የሚረግፈውን ፍሬ ቀምሶ ያጣጥማል። ዳኛቸው እንደሆን ማንም በጊዜው ያልተረዳው የቋንቋ ፈላስፋ ነው።

የአማርኛ ቋንቋን ስጋ በልቼ በመረቁ ያወራረድኩ ነኝ በማለት ስንኩራራ ድንገት 'ልቡስጥላ፣ ህግዘብ፣ ፍደሳ...' እያለ ባበሳ፤ በግድንግድ ቃላቱ ሲገርፈን ልክ እየገባን፤ እኚህን ባለማወቃችንም፤ እንዴት በማለት ከራሳችን ጋር እንፋጅ ይሆናል። የአደፍርሱ ዳኛቸው ግን ፤ አልበቃህ ብሎት የራሱን አዳዲስ የአማርኛ ቃላት በመፍጠር ላይ መሆኑ ነው። ደግነቱ ድረሱበት ሲል አጋፍጦ አይተወንም። እናስ? ስትሉ "ልቡስጥላ፣ በድብቅ ጭንቅላትዎችአችን ከልጅነት ጀምሮ እሚጠራቀምብን እምናውቀውን እምናየውን እምንወድድ እምንጠላውን ሁሉ የተሸከመ የመረጃ ቋት ነው። ያ እሚገነባው ከልጅነት ጀምሮ በምንሰማው፣ እምናደምጠው፣ እምንመለከተው፣ እምናነብበው፣ ከቤተሰብ ዙሪያ ሳለን እምንመለከተውን በአብነት በመቅዳት ነው" በማለት እያመራመረ ያስተምረናል።

አደፍርስም እንዲያው ነው፤ ሰብስቦ ማስተማር... እየተከራከሩ እውቀት መቃረም...ከትንሽ ትልቁ እየተጨዋወቱ የማህበረሰቡን አዕምሮ መሞረድ በፍቅር የሚወደው ነገር ነው። ከዘመኑ ቀድሞ የመጣ ዘመነኛ ጌጥም ነው። የሚያነሳቸው ርዕሰ ጉዳዮች የትየለሌ ናቸውና ጨዋታ አያልቅበትም። ታዲያ ጨዋታውን ናፍቀው አደፍርስን ፍለጋ ካለበት ድረስ መጥተው ልባቸው እስኪሰወር በጨዋታው ተመስጠው ሲያደምጡት ይቆዩና መልሶ ልባቸውን ውልቅ እያደረገባቸው በመሃል ጥለውት ሲሄዱም እንመለከታለን።

ቅኔ አዘል ያልተገለጡ መጋረጃዎች ያሉት በትምህርትና ምክሮቹ ውስጥ ብቻ ከመሰለን ብዙ ስተናል። በጨዋታዎቹ ውስጥ ሽንጥ የሚያደርጋቸው እልፍ ጉዳዮችም አሉ። ከመጽሐፉ በጥቂቱ ስንቀነጭብ፤

"እሺ ብሎ፤ እየቀጠለ፤ ተኝቼ ድምጽ ሰማሁ እና ስነቃ ጌቶች ስምአይጠሬን ሊጠሩ ነው ሲባባሉ ጓጉቼ ልመለከት ስነሳ የሆነ ነገር ጎትቶ በደረቴ ወደታች አነጠፈኝ። ስምአይጠሬ መስሎኝ ላየው ፈራሁ። ስጮኽ ሁለት እረኞች አጠገቤ አየሁ። አደፍርስ ሳታየው ጨረስክ እጅግ ሰነፍ ነህ አበቃ ወሬው 'ሞት እና ሕይወት ድንቁርናና እና ዕውቀት!' ብሎ ሁሌ እሚጠቅሳትን አባባል አቀረበ።

....

ዶሮውን ሴትዎች በማመራረጡ እንደሰው አመለካከቱ ሳይቀየር አንዴ የወደዳትን እንደእማይቀይረው እሚፀኑ አለመሆንአቸውን በላይ ሲያነሳ፤ አደፍርስ ሰው ከውጭአዊ እይታ በላይ ውስጥአዊ እይታዎች እንደአሉት ጨምሮ ገለጠ

...

በላይ ግን ገና መጀመሬ ነው ብሎ ቀጠለ። ፍግ ላይ ቁስዎችን ቆለሉ። ሰውዬው ስም እየጠሩ ሲያነብቡ፣ ሰዎቹ ቀምበጥ ከመያዝ እና በሀፍረትአቸው ቅጠል ከማስቀመጥአቸው በቀረ ምንም ሳይለብሱ ራቁት በቂጥአቸው አካባቢ ይጨፍሩ አለ"

በአደፍርስ፤ ዳኛቸው ኖሮ ያለፈበትንና እየኖረ ያለውን ዓለም ብቻ አይደለም ሊያሳየን የሚሞክረው። በኖርነውና በምንኖረው ድክርታም የሕይወት ዓለም ውስጥ ምንም የተለየ ነገር አለመኖሩን ስለተረዳ መጋረጃውን ገልጦ ከአድማስ ወዲያ ማዶ ሌላ ያልታየ ዓለምን ያስመለክተናል። ቀን ላይ ካለፍንበት ሀሩርና አሁን ካለንበት ጨለማ ይልቅ የነገዋን ጸሐያማ የማለዳ ጀንበር እንድንናፍቅ ዘንድ ይነግረናል።

በአደፍርስ ስሞች ለመጠሪያነት የሚያገለግሉ እንዲሁ ስም ብቻ አይደሉም። ቆም ብሎ በአዕምሮው ላሰናሰናቸው አንዳች ስውር እንፋሎት አዘል ናቸው። የራሱን የፈጠራ ቋጫ እየገመደ በፍካሬ አጋምዷቸዋል። አንዳንዴም ከሚስማር ላይ እንደሚያርፍ መዶሻ የጠነከሩ ሆኖ እናገኛቸዋለን። ጭሰኛው ገበሬ አቶ የየየየ፣አፍአዊ፣ ፍሬዋ ቀጫጫ፣ አባ ስብከት፣ ጎርፉ፣ ዋና ዳኛ ጥሶ በበረንዳው እና ሌሎችም መዶሻዎች ይገኙበታል።

ዳኛቸው እነዚህን እየተጠቀመ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ግብሮቻችንን ለማቅናት ክንዱን ሲያፈረጥም እናገኘዋለን። የሚከውነው ብዙ ነው። ይሞርድበታል፤እያረሰ ይዘራበታል፤ እያጨደ ይሰበስብበታል፤እየወቃ ያነፍስበታል። የተማረው ምርጡ ገበሬ፤ አደፍርስ ደግሞ ምርቱን ከግርዶ ለመለየት በገበሬ ማህበሩ የተገኘ፤ በዳኛቸው ተሹሞ በእውቀት ቅባት የተጠረገ አዲስና ልዩ የሆነ የብርሃን ፍኖት ነው። አንዳንዴም ከማህበረሰቡ ልማድና ወግ እያፈነገጠ ሊያመልጥ ሲል ከፊት በግንባሩ እየተጋጨ ሲወድቅ ሲነሳ እንመለከታለን። በዚህ ሁሉ የሚያስተምር ብቻም ሳይሆን የሚማርም ጭምር ነው። ሥልጣኔን፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ለውጥን ይሻል። የኛ የራሳችን የሆነውን ከዘመኑ ጋር ስለማወዳጀት እንጂ በባዕዳን ጫማ እግር ከተን መሬት ለመሬት እንድንጎተት አይፈልግም።

አደፍርስ የሚነግረን ብዙ ቢሆንም ይህችን ግን እህችን ግን እናድምጠው፤"ዛሬ፤ ከልጅአቸው ፍሬዋ ጋር ስለኢትዮጵያ መነጋገር የቀጠሉት ስለሀገር ማስተማሩን ሆኖ፤ መልካም ወግ፣ ልማድ እና ቅርስዎች ሀገርአችን እንዳላት እና ሥልጣኔ የግድ ከውጭ እንደእማይመጣ መክረው ነግረው እስአቸውም በሀገርአቸው እንደእሚኮሩ አሳውቀዋት እንድታጠና አበረታቷት።

....

ሁላችንም እኩል ባንሆንም፣ ከመሀከላችን የበላይ ወይም የበታች የለም። ሁሉም በገባው መጠን በምድር ይመላለሳል። በዚህ አጭር ከንቱ ኑሮ ሁለት ነገሮች እርግጥ ናቸው—ፍቅር እና ሞት። በፍቅር እየኖርን አንዴ ብቻ እንሙት። በቁም ከመሞት የከፋ ነገር የለም። ፍቅር አልባ ሕይወት በቁም ደጋግሞ መሞት ነው"

ዳኛቸው ወርቁ ብዕር ተፈጥሮ የቸረችው ስጦታው ነበር። ገና የ13 ዓመት ልጅ ሳለ "ያላቻ ጋብቻ ትርፉ ኀዘን ብቻ" የሚል ድንቅ ቲያትር በመጻፍ እውነተኛ የጥበብ ልጅነቱን አስመስክሮበታል። በርካታ ሥራዎችን የሠራ ቢሆንም፤ ከአደፍርስ ቀጥሎ ገዝፎ የሚታወቅበት ሌላኛው በእንግሊዝኛ ተጽፎ በብዙ የአውሮፓ ቋንቋዎች እስከመተርጎም የደረሰለት "ዘ ሰርቲንዝ ሰን" የተሰኘው መጽሐፉ ነው። መንታው ባይሆንም ልክ እንደ አደፍርስ ያለ ነው።

ዳኛቸው በሕይወቱ የመጨረሻዎቹ ሰዓታት በብዙ ነገሮች ደስተኛ አነበረም። ብቸኝነትና ቁዘማ እየተጫጫነው በዝምታ ተውጦ ነበር። ምናልባት ከአደፍርስ ጀምሮ የሻተውን ምኞት ለማየት አልቻለም ይሆናል። ከየካቲት 16 ቀን 1928ዓ.ም ከደብረሲና የጀመረው የሕይወት ጉዞ በኅዳር 22 ቀን በ 1987ዓ.ም በአዲስ አበባ ተገታ። ዳኛቸው፤አስክሬኑ ወደ ደብረሲና ተወሰደ። እንደሥራቸው ታላላቅ ሥራዎች ግን፤ ለአስክሬኑ እንኳን በቅጡ ሽኝት አልተደረገለትም ነበር። እሱ ሄዷል። እትብቱን ተቀብላ ወደ ሕይወት የሸኘችው ምድርም መልሳ በድን አካሉን ተቀበለች።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## መዝናኛዎችን በምልክት ቋንቋ የመደገፍ ጥረት

እየሩስ ተስፋዬ

መስማት የተሳናቸው ወገኖች ማንኛውንም ነገር መሥራት እንደሚችሉ ለማሳየት ሥራውን የጀመረው ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ነው:: መስማት የተሳናቸው የወጣቶች የውዝዋዜ እና የቴአትር ክበብ የሚል ስያሜ ይዞ የወረዳዎችን ደጃፍ መርገጥ ጀመረ:: «መሥራት እንችላለን፤ አሠሩን!» ብሎ ራሱን በሚገባ አስተዋወቀ:: በከተማ ደረጃ ብቻ ተወስኖ የተለያዩ መድረኮች ላይ በመገኘት የውዝዋዜ ሥራዎቹን ማቅረብም ቀጠለ:: በ2013 ዓ.ም ፍቃድ አግኝቶ ሥራውን ማስፋፋት ጀመረ:: እንሆ አሁን ሶስት ዓመት ተሻግሯል- ኢትዮ ሀበሻ መስማት የተሳናቸው ማህበር::

መስማት የተሳናቸው ከማኅበረሰቡ ጋር በቅንጅት የመሥራቱ ነገር እናሳ ሲሆንና በምን እንግባባለን? የሚል ስጋት ሲመጣ ማኅበሩ የተለያዩ ዝግጅቶችን በማዘጋጀት መስማት የተሳናቸው ልጆች ላሏቸውና ለሌሎች ወላጆች ግንዛቤ እየሰጠ ይገኛል::፣

ሲሳይ ተሰማ መስማት የተሳነው ወጣት ነው:: የኢትዮ ሀበሻ መስማት የተሳናቸው ማኅበር ሥራ አስኪያጅ እና የውዝዋዜ አሰልጣኝም ነው:: ሀይማኖት ተስፋዬ ደግሞ የማኅበሩ ጸሐፊ፣ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ፣ ተወዛዋዥ እንዲሁም ሙዚቃዎችን ወደ ምልክት ቋንቋ እየቀየረች መልዕክቶች ለሌሎች እንዲደርሱ በበጎ ፈቃድ ትሠራለች:: ቤተሰቦቿም መስማት የተሳናቸው ናቸው:: ይህንንኑ አምድ ለማዘጋጀትም በእኛና በሲሳይ መካከል ያሉትን ጥያቄ እና መልሶችን በምልክት ቋንቋ እንዲተረጎም አድርጋለች::

ሲሳይ እንደሚናገረው፣ በኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ሰዎች መዝናኛ ያስፈልጋቸዋል:: መዝናኛ ሲባል ደግሞ የቴሌቪዝን ፕሮግራም፣ ፊልም፣ የልጆች ፕሮግራም፣ ሙዚቃዎችና ሌሎችንም ያካትታል:: ታዲያ እነዚህን ተመልክተው እንዳይዝናኑ እና ቁምነገር ያላቸውን መልዕክቶች እንዳያገኙ ብዙዎቹ መዝናኛዎች በምልክት ቋንቋ የታገዙ አይደሉም::

ይህንን የሚሠራ የለምና በኪነ ጥበብ አማካኝነት የሚተላለፉ መልዕክቶች፣ የሙዚቃ መልዕክትና ሌሎችን መረጃዎች መስማት ለተሳነው ማኅበረሰብ እንዲዳረስ ዓላማ



ኢትዮ ሀበሻ መስማት የተሳናቸው የውዝዋዜ ቡድን፣

ያደረገው ማኅበሩ፤ የውዝዋዜ ሥራዎችን በተለያዩ መድረኮች ላይ ቀርቦ ታዳሚዎችን ከማዝናናት በሻገር መዝናኛዎችን አዘጋጅቶ ማቅረብ እንደሚቻል በተግባር እያሳየ ይገኛል::

በርግጥ መስማት የተሳናቸው መስማት አይችሉምና ሙዚቃውን እንዴት ሰምተውት ይደንሳሉ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: መናበብ ካለ ብዙ ነገር ማድረግ ይቻላል:: ሙዚቃዎችን ወደ ምልክት ቋንቋ በመቀየር የማይቻል የሚመስልን ነገር እንዴት መሥራት እንደሚቻል እነሲሳይ በተግባር አሳይተዋል::

ሲሳይ እንደሚገልጸው፣ ለሕፃናት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የምልክት ቋንቋ ነው:: ብዙኃኑ የሕፃናት የቴሌቪዥን ዝግጅቶችና ፊልሞች በምልክት ቋንቋ የታገዙ አይደሉም:: በምልክት ቋንቋ የሚዘጋጁት ደግሞ ለልጆች የሚሆኑ አይደሉም:: ‹‹በቋንቋቸው ቢሠራላቸው ግን ዓይናቸው ይሰማል ወይም ያዳምጣል:: እጃቸው ደግሞ ይናገራል::›› ስለዚህ በዚህ ላይ በሚገባ ትልቅ ሥራ መሥራት ይገባል:: ማኅበረሰቡ መስማት የተሳናቸው መሥራት አይችሉም የሚል የተሳሳተውን አመለካከት መቅረፍ ይቻላል:: ከውዝዋዜው በተጨማሪ የግንዛቤ ሥራዎችን ማኅበሩ መሥራት ይቀጥላል::

ከዚህ ቀደም ማኅበሩ 24 አባላት የነበሩት ሲሆን፤ አሁን ላይ ግን አስር ብቻ ቀርተዋል:: ለዚህም ከሩቅ ቦታ ለሚመጡ አባላት የትራንስፖርት የመክፈል አቅም አለመኖርና አንዳንድ ወላጆች ደግሞ ልጆቻቸውን ለመላክ ፈቃደኛ አለመሆናቸው በምክያትነት ይጠቀሳል:: ማኅበሩ በሀዋሳ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝና በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች በመንቀሳቀስ ሥራውን ያቀርባል:: መስማት የተሳናቸው ምንም መሥራት እንደሚችሉ ያሳያል:: በእግረ መንገዱ በየክልሉ ብዙ የምልክት ቋንቋ የማይችሉ ሞራላቸውን በመገንዘብ ሥራቸውን አጠናክረው ለመሥራት አቅድ አለው::

ኢትዮ ሀበሻ በተለያዩ መድረኮች ላይ ሙዚቃዎችን በምልክት ቋንቋ በመቀየር መስማት ለተሳናቸው ድራማ እና ቴአትር ይሠራል:: በቀጣይም ከፊልም ሠሪዎች ቢጋራ ለመሥራት ጅምር ሥራዎች መኖራቸውን ሲሳይ ይጠቁማል:: በተለያየ ቦታ መስማት የተሳናቸው ልጆች መኖራቸውን ከግንዛቤ በማስገባት፤ እንዲሁም መስማት የተሳናቸው ወጣቶች መድረስ የሚፈልጉት ቦታ ላይ እንዲደርሱ ለማስቻል ወላጆች፣ መንግሥት እና ሌሎችም ኃላፊነታቸውን መወጣት እንደሚኖርባቸው ያሳስባል::

መስማት የተሳናቸው የነገ የሀገር ተረካቢ ዜጋ ናቸው የሚለው ሲሳይ፤ ወላጆችም መስማት የተሳነው ልጅ ካላቸው ከመደበቅ ይልቅ አምነው መቀበል እና ለልጄ ምን ላድርግ? የምልክት ቋንቋ ልማር ? የሚሉትንና ሌሎች ማሟላት የሚገባቸውን ነገር በማሰብ ቢሠሩ ችግሮችን የበለጠ ለማቅለል እንደሚረዳ ይናገራል:: በአብዛኛው ቦታዎች ላይ የምልክት ቋንቋ አለመኖር ብዙ ችግሮች እንዲፈጠሩም ይጠቅሳል:: የትራንስፖርት አካባቢዎች ላይ የምልክት ቋንቋ ባለመኖሩ ወዴት እንደሚሄዱ የሚያመላክት ነገር ባለመኖሩ ሲቸገሩ እንደሚታዩም ይገልጻል:: በሕክምናና በሌሎች ተቋማትም ችግሩ ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ የምልክት ቋንቋ የግድ መስፋፋት እንዳለበት ያስረዳል::

ማኅበሩ የኪነጥበብ ሥራዎችን በመሥራት የግንዛቤ ሥራ እየሠራ የሚገኝ ሲሆን ፤ ድጋፎችን ቢያገኝ የበለጠ እንደሚሠራ ያምናል:: መስማት የተሳናቸው እንደሌላው ማኅበረሰብ የሚዝናኑበት ቦታ፣ቴአርትር ቤት፣ሲኒማ እና መሰል የመዝናኛ ቦታዎች ካልተዘጋጁላቸው ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ፣ ወደ ሱስ ሕይወት እንዲገቡ እና ወዳልተፈለጉ ድርጊቶች ሊያመሩ ይችላሉ:: ስለዚህም ወደ መጥፎ ነገር እንዳይሄዱ አመቺ የመዝናኛ አማራጮችን በማሟላት ማበረታታት ይገባል::

ከዚህ ቀደም «ዓለም አቀፍ መስማት የተሳናቸው ቀን» በኬንያ ሀገር ተከብሮ ውዝዋዜ እንዲያቀርቡ ለማኅበሩ ግብዣ ቢደረግለትም ስፖንሰር ባለማግኘታቸው ምክንያት ሥራቸውን ማቅረብ አልቻሉም:: ከዚህ በኋላም ቢሆን ሌሎች ግብዣዎች እንደሚኖሩ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ማንኛውም አካል ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ማኅበሩ ይጠይቃል::

ማኅበሩ አሁን እየሠራ ያለውን ሥራ ከማስፋፋት በተጨማሪ በቀጣይም መስማት የተሳናቸው የሚዝናኑበት ሲኒማ እና መሰል የመዝናኛ ስፍራዎችን ለመክፈት ውጥን ያለው በመሆኑ፤ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እና የአዲስ አበባ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እስካሁን ድረስ ላደረጉላቸው ድጋፍ ምስጋናውን ያቀርባል:: ሌሎችም ድጋፋቸውን እንዲያደርጉ ይጠይቃል::

# ዓለም አቀፍ

## ሳውዲ አረቢያ በአሜሪካ የተቋቋመው የቀይ ባሕር ዘብ ጥምረትን እንደማትቀላቀል ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሳውዲ አረቢያ በአሜሪካ የተቋቋመውን የቀይ ባሕር ዘብ ጥምረትን እንደማትቀላቀል ተገለጸ፡፡

ለፍልስጤም ነጻነት እታገላለሁ የሚለው ሐማስ ከ80 ቀናት በፊት በእስራኤል ላይ ያልተጠበቀ ጥቃት ማድረሱን ተከትሎ ጦርነት መቀስቀሱ ይታወሳል።

እስራኤል በወሰደችው የአጸፋ እርምጃ ከ20 ሺህ በላይ ፍልስጤማውያን ሲገደሉ ከአንድ ሺህ 200 በላይ እስራኤላውያንም ተገድለዋል።

የእስራኤልን የጋዛ ጥቃት ተከትሎ በርካታ ሀገራት እና ተቋማት ያወገዙ ሲሆን የየመኑ ሁቲ ታጣቂ ከእስራኤል ጋር ግንኙነት አላቸው ባላቸው መርከቦች ላይ ጥቃት በማድረስ ላይ ነው።

የሁቲን ጥቃት ተከትሎ የቀይ ባህር ትራንስፖርት አደጋ ላይ የወደቀ ሲሆን ይህን የዓለም ንግድ መሳለጫ መስመር ከአደጋ ለመጠበቅ በአሜሪካ የሚመራ የባሕር ኃይል ጥበቃ ቡድን ይሰማራል ተብሏል።

በአሜሪካ ይፋ የተደረገውን ይህን የሀገራት ጥምረት በርካታ ሀገራት እንደሚቀላቀሉ የገለጹ ሲሆን ብሪታንያ፣ ፈረንሳይ፣ ጣልያን፣ ግሪክ፣ ኔዘርላንድ እና ስፔን ዋነኞቹ ናቸው።

ይሁንና የቀይ ባሕር ትራንስፖርት ቅርብ የሆኑት ሳውዲ አረቢያ እና የተባበሩት አረብ ኢምሬቶች የአሜሪካንን ጥምረት እንዳልተቀላቀሉ ሮይተርስ ዘግቧል፡፡

እንደዘገባው ከሆነ ሁለቱ ሀገራት በአሜሪካ አስተባባሪነት ይፋ የተደረገው የቀይ ባሕር ጥበቃ ጥምረትን ያልተቀላቀሉት ለዓመታት የዘለቀው የየመን ጦርነት እንዳያገረሽ፣ ከኢራን ጋር በቅርቡ የጀመሩት መልካም ግንኙነት እንዳይበላሽ እና በመጀመሪያ እስራኤል የጋዛ ጦርነትን እንድታቆም ስለሚፈልጉ ነው ተብሏል፡፡

የየመን ሁቲ አማጺያን በበኩሉ እስራኤል በጋዛ የጀመረችውን ጥቃት ካላቆመች በቀይ ባሕር ላይ ጥቃት ማድረሱን እንደሚቀጥል አስታውቋል።

እንዲሁም የእስራኤል ጥቃት የሚቀጥል ከሆነ የአሜሪካ መርከቦችን ማጥቃት እጀምራለሁ ሲልም አማጺያኑ አስታውቋል፡፡

የሁቲ አማጺያን ከእስራኤል ጋር ግንኙነት አላቸው ያላቸውን መርከቦች በሚሳኤል እና ሰው አልባ አውሮፕላን ማጥቃቱን ተከትሎ በርካታ የዓለማችን የሎጅስቲክስ ድርጅቶች በቀይ ባሕር መጓዝ በማቆም ላይ ናቸው፡፡



## ፕሬዚዳንት ሺ “ታይዋንን ከቻይና ለመነጠል የሚደረግ ማንኛውንም ሙከራ እናስቆማለን” አሉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የቻይናው ፕሬዚዳንት ሺ ጂንፒንግ “ታይዋንን ከቻይና ለመነጠል የሚደረግ ማንኛውንም ሙከራ እናስቆመዋለን” ሲሉ ተናግረዋል።

ፕሬዚዳንቱ ይህን አስተያየት የሰጡት ታይዋን ከሁለት ሳምንት በኋላ ለምታደርገው ፕሬዚዳንታዊ እና የፓርላማ አባላት ምርጫ የደሴቷ ቀጣይ እጣ ፈንታ የምርጫ ቅስቀሳ አካል መሆኑን ተከትሎ ነው።

የታይዋን ምርጫ የውስጥ ጉዳዬ ነው ያለችው ቤጂንግ፤ በፕሬዚዳንታዊ ምርጫው ሰፊ የማሸነፍ እድል ያላቸውን የዴሞክራቲክ ፕሮግረሲቭ ፓርቲ ተወካይ ላይ ቺንግቲ “አደገኛ አስገንጣይ” ናቸው በሚል አውግዛቸዋለች።

የገዥው ዴሞክራቲክ ፕሮግረሲቭ ፓርቲ ዋነኛው ተቀናቃኝ ኩሚንታንግ ፓርቲም ከቻይና ጋር ጥብቅ ወዳጅነት መመስረትን የሚደግፍ ቢሆንም የደሴቷ እጣፈንታ በሕዝቦቿ ይወሰናል የሚል አቋም ይዟል።

ከሁለት ሳምንት በኋላ በሚደረገው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ አሸንፎ ስልጣን የሚይዘው አካል ከቤጂንግ ጋር መፋጠጡ አይቀርም የሚለው የሬውተርስ ዘገባም፤ በታይዋን ሰርጥ ዳግም ውጥረት ሊነግስ እንደሚችል ጠቁሟል።

ፕሬዚዳንት ሺ ጂንፒንግም “የታይዋን እና ቻይና ውህደት አይቀሬ ነው፤ ታይዋንን ከእናት ሀገሯ የመነጠል ሙከራንም እንከላከላለን” ማለታቸውን ሽንዋ ዘግቧል።

ቤጂንግ እንደሉአላዊ የግዛቷ አካል የምትቆጥራትን ታይዋንን ለመገንጠል የሚደረጉ ሙከራዎችን በኃይል ልታስቆም እንደምትችል ግን አልጠቀሱም።

ባለፉት 18 ወራት ሁለት ግዙፍ ወታደራዊ ልምምዶችን በታይዋን አቅራቢያ ያደረገችው ቻይና፥ ወደ ታይዋን ሰርጥ የጦር አውሮፕላኖቿን እና መርከቦቿን ስትልክ ሰንብታለች።

ታይዋን እንደ ሉአላዊ ሀገር ከአሜሪካ እና ሌሎች ምዕራባውያን ሀገራት ጋር ወታደራዊ ግንኙነት ለመመስረት መሞከሯና ዋሽንግተን ለደሴቷ የጦር መሳሪያ ለመሸጥ መስማማቷ ውጥረቱን ማባባሱም ይታወሳል።



ታይዋን ከምዕራባውያን ጋር የመሰረተችው ወዳጅነት በቻይና የሚወደድ አልሆነም

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቀምላቸው አበበ ይማም (ሞሺ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ላለመስማማት መደራደር...

ከገጽ 5 የዞረ

ድርሻዋን እና ብሔራዊ ደህንነቷን የመጠበቅ መብቷ የተጠበቀ ነው" ብሏል።

ኢትዮጵያ በበኩሏ ይህ ግብፅ ከድርድሩ መጠናቀቅ በኋላ ያወጣችው መግለጫ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ቻርተር እና የአፍሪካ ኅብረት ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌን የሚጻረር ነው በማለት መግለጫውን እንደማትቀበለው አስታውቃለች። ኢትዮጵያም የቅኝ ግዛቱን ውል እንደማትቀበለው ደጋግማ አሳውቃለች። ሀገራችን ይሄን አስገዳጅ ስምምነት አደረገች ማለት እኤአ ዘመን አቆጣጠር በ1929 እና በ1959 ዓ.ም ግብጽና ሱዳን የተፈራረሙትን የቅኝ ግዛት ሕግ ተቀበለች ማለት ነው።

የመጀመሪያው ስምምነት የታላቁ የአባይ ወንዝ መነሻ የሆነችውንና 77.5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ወይም 86 በመቶውን የምታበረክተውን ሀገራችንና ሌሎች ስምንት የግርጌ ተፋሰስ ሀገራትን ያገለለ ነው። በዚህ ኢፍትሐዊ ስምምነት ግብጽ 48.5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ለመጠቀም ፤ ሱዳን ደግሞ 4 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ለመጋራት ተስማምተዋል። ሀገራችንን ጨምሮ ለራስጌ ሀገራት የተውት ጠብታ ውሃ የለም። ጉድ እኮ ነው።

ሁለተኛውና የፈርኦን እብሪት ግዘፍ ነስቶ የተገለጠበት ስምምነት ደግሞ ፣ "ከግብፅ መንግሥት ፈቃድ ውጭ የውሃ መጠኑን ሊቀንስ የሚችል የመስኖም ሆነ የኃይል ማመንጫ ሥራዎችን በአባይ ገባሮችና ሀይቆች ላይ መገንባት አይቻልም::" የሚል ነው። እነዚህን የቅኝ ግዛት ውሎችን ሀገራችን እንዴት ትቀበላለች ተብሎ ይጠበቃል። በነገራችን ላይ ይሄን አስገዳጅ ስምምነት ተፈራረሚ ማለት ግብፅ የህዳሴው ግድብ 40 ቢሊዮን ኪዩቢክ ውሃ በየዓመቱ ይልቀቅ በሚል ያቀረበችውን ግዴታ መንግሥት ከመቀበሉ ባሻገር ኢትዮጵያ ከህዳሴው ግድብ በኋላ በዓባይ ወንዝ ላይም ሆነ በገባሮቹ ምንም ዓይነት ልማት እንደማታካሂድ በመስማማት ሉዓላዊነቷን አሳልፋ ልትሰጥ ነው ማለት ነው።

በእጅ አዙር የውሃ ክፍፍል ስምምነቱን ተቀበለች፤ ለሚቀጥሉት ዓመታት ከህዳሴ ግድቡ በየዓመቱ የሚለቀቀው የውሃ መጠን ምን ያህል እንደሚሆን ተስማሚ ማለት ነው። መንግሥት ይሄን አስገዳጅ ስምምነት ይቀበል ማለት የዓባይ ውሃ ምንጭና ተፈጥሯዊ ባለቤት የሆነችውን ኢትዮጵያን ያግልል በተጨማሪ ኢትዮጵያ ምንም ዓይነት የውሃ ድርሻ የላትም ማለት ነው። ግድቡን በጋራ እናስተዳድረው የሚለው ሌላው የግብጽ ደባና ጥያቄ በዚህ አሳሪ ስምምነት ይካተት አይካተት ወደፊት አብረን የምናየው ይሆናል።

ለናይል ወንዝ 86 በመቶ ውሃ የምታበረክተው ኢትዮጵያ ፍትሐዊ በሆነ አግባብ ውሃውን የመጠቀም መብቷ ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም:: ሀገራችን አስገዳጅ ስምምነቱን ፈረመች ማለት ፤ በተዘዋዋሪ መንገድ ግጭትንና አለመግባባትን ለመፍታት ሰባቱ የራስጌ የተፋሰስ ሀገራት የቅኝ ግዛት ዘመን ስምምነቶች ፍትሐዊ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አዳዲስ ውሎች ሊተኩ እንደሚገባ የሚጠይቀውና በ2002 ዓ.ም የተፈረመውን የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት Co-operation Framework Agreement (CFA) አፈረሰች ማለት ነው።

ስምምነቱን የተፈራረሙ ሀገራትን ብሩንዲ፣ ኬንያ ፣ ኡጋንዳ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ታንዛኒያና ሩዋንዳ ካጂ ፤ የትብብር ማዕቀፉ የናይልን ወንዝ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መጠቀምን የሚያረጋግጥና ዋስትና የሚሰጥ ቋሚ ኮሚሽን እንዲቋቋም የሚጠይቀውን ስምምነት ተቃረኒ ማለት ስለሆነ ሀገራችንን እንደማትቀበለው በተደጋጋሚ አቋሟን አሳውቃለች::

ዳሩ ግን ሱዳንና ግብፅ ይህን የትብብር ማዕቀፍ ለመፈረም ፈቃደኛ ባይሆኑም በ2007 ዓ.ም በግብፅ፣ በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የተፈረመውን የመርሆዎች መግለጫ (Declaration of Principles) ፈርመዋል:: በዚህ ስምምነት ሱዳንና ግብፅ የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክትን የተቀበሉ ሲሆን ኢትዮጵያም ግድቡ በግርጌ ተፋሰስ ሀገራት ማለትም በግብፅና በሱዳን ሊያሳድረው የሚችል ተፅዕኖ ወይም ጉዳት ካለ ጥናት እንዲደረግ ተስማምታለች:: በዚህ ስምምነት ላይ ተከታታይ ውይይቶች የተካሄዱ ሲሆን ተስፋም ተጥሎባቸው ነበር::

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ለቀጣናዊ ትብብር አብነት የሚሆንና የራስጌ ሀገራትን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት ስለሆነ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ድጋፍ ሊደረግለት ሲገባ ግንባታን መም የራስጌ ተፋሰስ ሀገራትን ብሔራዊ ጥቅም የሚጎዳ ነው :: ይልቁን ግብፅም በግድቡ ውሃ አሞላል ላይ ከኢትዮጵያ ጋር ጀምራ ወደነበረው ድርድር ብትመለስ ሀገራቱን ተጠቃሚ ማድረግ የሚችል መግባባት መድረስ ይችላል ::

ምክንያቱም ስምምነቶቹ የተፋሰስ ሀገራትን በተለይ ሀገራችንን ያላሳተፉ ከመሆኑ ባሻገር ስምምነቶቹ የመንግሥታቱ ድርጅት እኤአ በ1997 ይፋ ካደረገው የወንዞች የፍትሐዊ ተጠቃሚነት ድንጋጌ ጋር ይጣረሳሉ :: ሆኖም የራስጌ የፋሰሱ ሀገራት የጋራ የሆነውን የዓባይ የውሃ ሀብት ለማልማት የግብፅ ፍቃድ አያስፈልጋቸውም:: ሱዳንና ግብፅ ዓባይን ለትላልቅ መስኖዎችና የኃይል ማመንጫነት ሲጠቀሙበት በአንጻሩ ሌሎች የራስጌ ተፋሰስ ሀገራት ወንዙን የሚጠቀሙበት ለአነስተኛ ኃይል ማመንጫነት ብቻ ነው::

ይህ የሆነበት ምክንያት የጋራ የሆነውን ሀብት በስፋት አልምተው የመጠቀም ፍላጎት ስለሌላቸው ሳይሆን ዓለምአቀፍ የፋይናንስ ተቋማት በግብፅ ተፅዕኖ የተነሳ ብድር የመስጠት ፍላጎት ስለሌላቸው ነው:: የተፋሰሱ ሀገራት የሕዝብ ብዛት በከፍተኛ ፍጥነት በመጨመር ላይ መሆኑን ተከትሎ የውሃ፣ የምግብና የኃይል ፍላጎታቸው በእጅጉ እያሻቀበ ነው::

የሚያሳዝነው እነዚህ ፍትሐዊ ያልሆኑ የፋይናንስ ተቋማት ለግብፅ ሲሆን እጃቸው ይፈታል:: በዚህም ጭው ባለ በረሃ ግዙፍ መስኖዎችን ፣ ሀገሪቱን ሙሉ በሙሉ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ያደረጉ ትላልቅ የውሃ ኃይል ማመንጫዎችን ገንብተዋል:: በስተሰሜን የሱዳንና ግብፅ ድንበር ላይ ግብፅ በዓለማችን ረጅሙን የዓባይ ወንዝ በመገደብ በግዙፍነቱ ከዓለም 3ተኛ የሆነውን የአስዋን ግድብ ገንብተዋል::

የአስዋን ግድብ 10 ዓመት ከፈጀ ግንባታ በኋላ እአአ በ1970 ተጠናቋል:: በ1954 ግብፅ ከዓለም ባንክ ብድር ፣ ከአሜሪካ ደግሞ ርዳታ ለማግኘት ጠይቃ ተስፋ ተሰጧት የነበር ቢሆንም ከእስራኤል ጋር በገባችበት ውዝግብ የተነሳ ሳይሳካ ቀርቷል:: በዚህ የተከፋችው ግብፅ ወዲያው ፊቷን ወደ ሶቪየት ሕብረት በማዞር ባገኘችው ብድር ግንባታውን ማካሄድ ችላለች::

ግድቡ 90ሺህ ሱዳናውያን ከማፈናቀሉ ባሻገር በቅርስነት ተከልለው የነበሩ ቦታዎችም በውሃ ተውጠዋል:: እነዚህ ተፈናቃዮች ከቀዬአቸው 600 ኪሎ ሜትር ርቀው እንዲሰፍሩ ሲደረግ ፤ በግድቡ የተነሳ ከቀዬአቸው የተፈናቀሉ ግብጻውያን ግን 40 ኪሎ ሜትር ብቻ እርቀው እንዲሰፍሩ ተደርጓል:: ግብፅ ይህን ግዙፍ ግድብ ስተገነባ ከሱዳን ውጭ ሌሎች ሀገራትን ማማከር አይደለም እወቁልኝ እንኳ አላለችም:: ሱዳንንም ያማከረቻት አስባላት ሳይሆን በዜጎቿ ላይ የምትፈፅመውን ግፍ እንድታውቀው ይመስላል::

የአስዋን ግድብ 2ሺህ 100 ሜጋ ዋት በማመንጨት ማለትም ግማሹን የሀገሪቱን የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎት ያሟላ ሲሆን ለከፍተኛ መስኖ ልማትም ውሏል:: ግብፅ እምቅ የኃይል አማራጭ ቢኖራትም ከውሃ የኃይል ማመንጫዎች ውጭ የመጠቀም ፍላጎት የላትም:: አንዳንድ ምንጮች እንደሚጠቁሙት 4 ነጥብ 4 ቢሊዮን በርሚል የነዳጅ ድፍድፍ ክምችት በምድሯ ቢኖርም በቀን እያመረተች ያለው ከ 640ሺህ በርሚል በታች ነው ::


የተፈጥሮ ጋዝ ክምችቷ ወደ 2 ነጥብ 2 ትሪሊዮን የሚጠጋ ኩም የሚጠጋ ሲሆን እያመረተች ያለው ግን ወደ 60 ቢሊዮን ኩም የሚጠጋ ብቻ ነው:: እንዲሁም 547ሺህ 500 በርሚል በቀን የተጣራ ነዳጅ ታመርታለች :: ሰፊ የከርሰ ምድር ውሃ እንዳላትም ጥናቶች ያመለክታሉ:: ይህ ሁሉ አማራጭ የኃይልም ሆነ የመስኖ ሀብት እያላት መላው ስስቷና ቀልቧ ዓባይ ላይ ነው::

ግንባር ያድርገው ብላ በየአደባባዩ እየማለች ፣ እየተገዘተችና እየካደች ፤ ኢትዮጵያ ዝናብን ጨምሮ በርካታ አማራጭ የውሃ ሀብት እያላት ጥቁር አባይ ላይ ግድብ የምትገነባው ግብፅን ለማንበርከክና ጂኦ ፖለቲካዊ ሚዛኗን ለመጨመር ነው ስትል በየመድረኩ የአዞ እንባዋን እየረጨች ነው::

**ሻሎም ! አሜን ።**

**የመጀመሪያው ስምምነት የታላቁ የአባይ ወንዝ መነሻ የሆነችውንና 77.5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ወይም 86 በመቶውን የምታበረክተውን ሀገራችንና ሌሎች ስምንት የግርጌ ተፋሰስ ሀገራትን ያገለለ ነው**

# ስፖርት



## የባሕርዳር ስታድየም ግንባታን ለማጠናቀቅ የተወሰደ ትልቅ ርምጃ

ቦጋለ አበበ

ባለፉት 15 ዓመታት የሀገሪቱን እግር ኳስ ወደ አንድ ደረጃ ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ግዙፍ ስታዲየሞች ግንባታ በተለያዩ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ቢጀመሩም አንዳቸውም መጠናቀቅ አልቻሉም።

ለዓመታት ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ሲያስተናግድ የነበረው የአዲስ አበባ ስታዲየምም ከሶስት ዓመት በፊት ዓለም አቀፍ ጨዋታዎችን ከማስተናገድ መታገዱን ተከትሎ እየታደሰ የሚገኝ ሲሆን ዛሬም ድረስ ተጠናቆ ወደ ሥራ መግባት አልቻለም፡፡ በ2006 ዓ.ም ግንባታው በከፊል ሳይጠናቀቅ የመላ ኢትዮጵያ ጨዋታዎችን በማስተናገድ ወደ ሥራ የገባው የባሕርዳር ስታዲየም የብሔራዊ ቡድንና የክለቦች በርካታ ዓለም አቀፍ ጨዋታዎች ሲያስተናግድ ቢቆይም የካፍ መመዘኛ መስፈርትን ሙሉ በሙሉ ባለማሟላቱ ከጥቅምት 2014 ዓ.ም አንስቶ ተመሳሳይ እገዳ ተጥሎበታል።

በዚህም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የባሕርዳር ስታድየም ከታገደ ወዲህ የአፍሪካ ዋንጫና የዓለም ዋንጫ ጨዋታዎችን ለማድረግ ወደሌሎች ሀገራት ለመሰደድ ተገዷል። የባሕርዳር ስታድየም በካፍ ጨዋታዎችን እንዳያስተናግድ ከታገደ ጀምሮ የክልሉ መንግሥት መሟላት ያለባቸውን መሰረተ ልማቶች ለማሟላት ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን በተደጋጋሚ ገልጿል። ያም ሆኖ ስታድየሙ አስፈላጊውን ዓለም አቀፍ መስፈርት አሟልቶ ሳይጠናቀቅ ዓመታት ተቆጥረዋል።

አሁን ግን የክልሉ መንግሥት ስታድየሙን በተቻለ ፍጥነት ለማጠናቀቅ ወይም አስፈላጊውን መስፈርት እንዲያሟላ ለማድረግ ተጨማሪ በጀት ከማፅደቅ በተጨማሪ የተለያዩ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል። ከነዚህም ሥራዎች መካከል በስታድየሙ 52 ሺ ዘመናዊ ወንበር ለመግጠም ተቋራጭ ተለይቶ ወደ ሥራ መገባቱን የክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ከትናንት በስቲያ ይፋ ማድረጉን አሚኮ ዘግባል። ይህም ሳይጠናቀቅ ዓመታት እያስቆጠረ የሚገኘውን ስታድየም ለማጠናቀቅ የተወሰደ ትልቅ ርምጃ ሆኗል፡፡



ስታድየሙ ሲጠናቀቅ 60 ሺ ተመልካቾችን በወንበር ማስተናገድ ይችላል ተብሎ ይጠበቃል፣

የወንበር ገጠማ ሥራውን የሚያከናውነውም በሜድሮክ ኢትዮጵያ ሥር ያለ "አዲስ ጋዝ" የተሰኘ ንዑስ ተቋራጭ መሆኑ ተጠቁሟል። ለወንበር ገጠማው የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችም ከቻይና ወደ ሀገር ውስጥ መምጣታቸው ታውቋል፡፡ የሚገጠመው ወንበር የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) እና የዓለም አቀፉን እግር ኳስ ማኅበር (ፊፋ) የደረጃ መስፈርትን ያሟላ እንደሚሆንም ተጠቁሟል።

የክልሉ መንግሥት ባለፈው ሳምንት ለስታድየሙ ግንባታ ማጠናቀቂያ ከ970 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት መፍቀዱ ይታወሳል። የስታድየሙ ግንባታ የቀሪ ሥራዎች ማጠናቀቂያ አንድ ቢሊዮን ብር በጀት ተጠይቆ የነበረ ሲሆን ከ970 ሚሊዮን ብር በላይ ነው የተፈቀደው። ከተፈቀደው ገንዘብ 400 ሚሊዮን ብር በሩብ ዓመቱ ሥራ ላይ መዋሉም ታውቋል።

የባሕር ዳር ስታድየም የዓለም አቀፉ የእግር ኳስ ማኅበር (ፊፋ) መመዘኛዎችን መሰረት በማድረግ ቀሪ ግንባታውን የማጠናቀቅ ሥራ ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ እንደሚጠይቅ ከዚህ ቀደም የተገለፀ ሲሆን፤ የማጠናቀቂያ ሥራዎችም ከዓመት በፊት መጀመራቸው ይታወቃል፡፡

የስታዲየሙ ሁለተኛ ዙር የግንባታ ሥራዎች ባለፈው ዓመት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በፈቀደው 700 ሚሊዮን ብር የተጀመረ ሲሆን፤ ቀሪው 300 ሚሊዮን ብር ደግሞ በሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ድጋፍ እንደሚሸፈን በወቅቱ ተገልፆ ነበር፡፡

በሁለተኛው ዙር የስታድየሙ ግንባታ ከሚሠሩ ሥራዎች መካከል የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳ ጥራት ማሻሻያ፣ የእንግዳ መቀበያ ክፍል፣ መቀመጫ ወንበር መግጠም እና መሰብሰቢያ አዳራሽ እንደሚገኙበት ተገልጿል፡፡

የማጠናቀቂያ ሥራው የፊፋ መመዘኛ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ የሚሠራ ሲሆን፤ ይህም ስታድየሙ ዓለም አቀፍ ጨዋታዎችን ወደ ማስተናገድ እንዲመለስ ያስችለዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡የሁለተኛው ዙር ግንባታ በአንድ ዓመት ጊዜ እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል፡፡


## የአማካሪዎች የፍላጎት መግለጫ /EXPRESSION OF INTEREST FOR CONSULTANCY SERVICE/
## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

የደ/ብርሃን ከተማ አስተዳደር ከተማ መሰረተ ልማት መምሪያ ግዥና ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ቡድን በከተማው በጀት የካፒታል መዋዕለ ነዋይ እቅድ /CIP/ በዚህ በጀት ዓመት ሎት 1 የአስፋልት መንገድ ዲዛይን ስራ ዶክመንት ዝግጅት የማማከር አገልግሎት (Aspalt Road Design and Bid document preparation) እና የግንባታ ቁጥጥር የማማከር ስራ ለማሰራት በአርክቴክቸር፣ ኮንስትራክሽን እና ተያያዥ ጉዳዮች የማማከር ስራዎች ወይም በኮንስትራክሽንና ተያያዥ ስራዎች የማማከር አገልግሎት ወይም በከተማ ፕላን፣ አርክቴክቸር፣ ሲቪል ኢንጂነሪንግ እና ተያያዥ ስራዎች የማማከር አገልግሎት የንግድ ስራ ፈቃድ አማካሪዎችን /short list/ በማድረግ አወዳድሮ ለማሰራት ይፈልጋል፡፡

የስራው ዓላማ፡- ለተጠቀሱት ስራ የአስፋልት መንገድ ዲዛይን እና የግንባታ ቁጥጥር የማማከር ስራ መስራት ይሆናል፡፡ ዝርዝር ስራዎች በቢጋር /TOR/ ላይ እና በመወዳደሪያ ሃሳብ ማቅረቢያ /Request for proposal / ሰነድ ውስጥ ተዘርዝሮ ቅድመ መረጣውን ለሚያልፉ ተወዳዳሪዎች /short listed firms/ ይሰጣል፡፡

በመሆኑም ከላይ በተጠቀሰው ስራ ላይ ለመወዳደር ፍላጎት እና በቂ ልምድ ያላችሁ ቅድመ መረጣ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ማስረጃዎች በማቅረብ ፍላጎታችሁን እንድትገልፁ ይጋብዛል፡፡

1. በ2016 በጀት ዓመት የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸው
2. የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/ ከፋይነት የተመዘገቡ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ ያላቸው፡፡
3. ከዚህ በፊት በዲዛይን ስራ እና በግንባታ ቁጥጥር ስራ የማማከር አገልግሎት በቂ ልምድ ያለው ለመሆኑ ማስረጃ ሊያቀርብ የሚችል፡፡
4. ለማማከር ስራ ሊያሰማራቸው የሚችሉ ቁልፍ ባለሙያዎች ያሉት እና የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምዳቸውን ማስረጃ የሚያቀርቡ፤
5. ሌሎች ለቅድመ መረጣ ወይም ውድድር ላይ ያግዛሉ የሚባሉ የድርጅቱን የመፈፀም አቅም ደረጃ መሳሪያና ቁሳቁስ የሚያስረዱ ማስረጃዎችን የሚያቀርብ፡፡
6. ስራውን ለመስራት ፍላጎት ያለው አማካሪ ድርጅት ከላይ የተዘረዘሩትን ማስረጃዎችን በየገፁ የደርጅቱ ማህተም ተደርጎበት ከማመልከቻ ጋር ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ የድርጅቱ ህጋዊ ማህተም ያልተደረገበትና ማመልከቻ የሌለው የፍላጎት መግለጫ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
7. ይህ የፍላጎት መግለጫ /Expression of interest/ ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ በታሸገ ፖስታ በደ/ብርሃን ከተማ አስተዳደር ከተማ መሰረተ ልማት መምሪያ ግዥና ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ቡድን 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 15 ማስረከብ ይኖርባቸዋል፡፡ ጨረታው የቅድመ መረጣው ሥራ ማስታወቂያ በወጣበት በ16ኛው ቀን እስከ 4፡00 ሰዓት ድረስ ማስገባት አለባቸው፡፡ በዚሁ ቀን ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ቅድመ መረጣ /short list firms/ ማድረግ ይጀመራል፡፡ ዕለቱ ቅዳሜ እና እሁድ ወይም የህዝብ በዓላት ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ይከፈታል ቅድመ መረጣው እንደተጠናቀቀ ቅድመ መረጣውን ላለፉትና ለተመረጡት /short list/ የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ሰነድ ይሰጣቸዋል፡፡
8. የፍላጎት መግለጫ ሰነዱ በድርጅቱ ህጋዊ ማህተም የተረጋገጠ መሆን አለበት ስርዝ ድልዝ መኖር የለበትም፡፡
9. መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ የፍላጎት መግለጫ ማስታወቂያውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብት አለው፡፡

ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ ከሰኞ እስከ አርብ ባሉት የስራ ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት መጠየቅ ይችላሉ፡፡

### የደ/ብርሃን ከተማ አስተዳደር ከተማ መሰረተ ልማት መምሪያ